# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 284 ሰኔ 14 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# ለዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ ሰባት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኞች ተዘጋጅተዋል

- በአንድ ጀንበር 150 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዷል
- ዛሬ የቅድመ ማስጀመሪያ መርሀ ግብር ይከናወናል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ለ2016/17 የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር የአረንጓዴ አሻራ ሰባት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኞች መዘጋጀታቸውን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በአንድ ጀንበር 150 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ዕቅድ መያዙም ተመላክቷል፡፡

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ኢያሱ ኤልያስ (ፐ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለ2016/17 የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በሀገር አቀፍ ደረጃ ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞችን ለማዘጋጀት ታቅዶ ሰባት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኞችን በማዘጋጀት ከእቅድ በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

አጠቃላይ ከተዘጋጁት ሰባት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን

ለዘንድሮው የአረንጓዴ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ አክሊሉ ታደሰ

## ከዓለም አቀፍ ባለሀብቶች በተለየ ለሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ልዩ ዕድል ተዘጋጅቷል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ከዓለም አቀፍ ባለሀብቶች በተለየ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ልዩ እድል መዘጋጀቱን የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን አስታወቀ። በአሥራ ሦስት ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከሚገኙ ኢንቨስተሮች ውስጥ 55 በመቶው የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች እንደሆኑም ተገልጿል።

ከ70 በላይ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የተሳተፉበት "መሬታችን ለባለሀብቶቻችን" በሚል መሪ ሃሳብ በኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የተዘጋጀ የንቅናቄ

ከዓለም አቀፍ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አምባሳደር ነብዩ ተድላ

## ኢትዮጵያ በብሪክስ ማዕቀፍ ንቁ ተዋናይ እየሆኑ ከመጡ ሀገራት አንዷ ሆናለች

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በብሪክስ ማዕቀፍ ውስጥ ንቁ ተዋናይ እየሆኑ ከመጡ ሀገራት መካከል አንዷ ሆናለች ሲሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቃል አቀባይ አምባሳደር ነብዩ ተድላ ገለጹ፡፡

ኢትዮጵያ በብሪክስ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ቴክኒክና ሙያ - የኢኮኖሚ ዕድገት ሞተር

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

ቴክኒክና ሙያ የአዕምሮና እጅ ጥበብ ውጤቶች የሚፈልቁበት ዘርፍ ነው፡፡ ይህን ዘርፍ የሀገርን ኢኮኖሚ በተገቢው ልክ እንዲደግፍ ለማስቻል የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

ዜጎችን በተለያየ መስክ የሙያ ባለቤት እና የፈጠራ ምንጭ ያደረገ የስልጠና ዘርፍ እንደመሆኑ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የዕድገት ሞተር ለማድረግ የተሠሩ ሥራዎችን መዳሰስ ተገቢ ይሆናል፡፡

የቴክኒክና ሙያ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ብሩክ ከድር (ዶ/ር) የስልጠና ዘርፉ ለአንድ ሀገር ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ወሳኝ ሚና የሚጫወት፤ ለኢንዱስትሪው መስክ ደግሞ ቀኝ እጅ ነው ይላሉ፡፡

ዘርፉ የሚያፈራው የሰው ኃይል ከኢንዱስትሪው ጋር ቀጥታ ግንኙነት እያለው እንኳን ይህን ሚናውን ያገናዘበ ትኩረት ሲሰጠው አልነበረም ባይ ናቸው፡፡

የመንግሥት ትኩረት በተለያዩ ጊዜያት እየተሻሻለ መምጣቱን የሚገልጹት ዳይሬክተሩ፤ በተለይ ከጣሊያን ወረራ ወዲህ ተግባረ ዕድ የቴክኒክ ትምህርት ቤት 1942

ቴክኒክና ሙያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# በኦሮሚያ ክልል የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ላይ የተሰጠው ትኩረት ተጨባጭ ውጤት እያስገኘ ነው

## - በክልሉ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር ላይ የከብቶች መኖ እየለማ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



ቦረና፡- በኦሮሚያ ክልል ቆላማና ደጋማ አካባቢዎች የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ላይ የተሰጠው ትኩረት ተጨባጭ ውጤት እያስገኘ መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በክልሉ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር ላይ የከብቶች መኖ ዓይነቶች እየለማ ነው።

የኦሮሚያ ክልል የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ ጨምሮ ሌሎች የቢሮው ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች በመገኘት የተለያዩ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ፣ ማራቢያና በሰው ሰራሽ ዘዴ ማዳቀያ ማዕከላትን ጎብኝተዋል።

የኦሮሚያ ክልል የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ በጉብኝታቸው ወቅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ደጋማና ወይና ደጋ አካባቢዎች በሰው ሰራሽ ዘዴ ላሞችን በማዳቀል የተሻለ ምርት የሚገኝበት ዝርያ ማባዛት ተችሏል። ቆላማ አካባቢ ላይ ደግሞ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያና ማራቢያ ማዕከላት ላይ እየተሰራ ይገኛል።

እንደ አቶ ጌቱ ገለጻ፤ የቦረና ዳልጋ ከብቶች ዝርያ ማሻሻያና ማራቢያ ማዕከል በድርቁ ጊዜ ከነበረበት አስጊ ሁኔታ ወጥቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የዳልጋ ከብቶችን ቁጥር ከ437 በላይ ማድረሱ ለዚህ ማሳያ ነው። ማዕከሉ በዕውቀት እንዲመራ መደረጉ ዳልጋ ከብቶቹ ጤናቸው ተጠብቆ ወደ ህብረተሰቡ እንዲደርሱ ከማድረግ ጎን ለጎን ባለሙያዎቹ ጥናቶች እንዲያደርጉ ያግዛል።

አቶ ጌቱ አክለውም፤ ማዕከሉ በኦሮሚያ ክልል ብቻ ሳይሆን እንደሀገር ትልቅ ዝርያ ማሻሻያ ነው ያሉ ሲሆን፤ በክልሉ በተለይ በቆላማ አካባቢዎች የመኖ ማቅረብ ሥራ ተሠርቷል። ግድቦች በመገደብም የውሃ እጥረት እንዳይከሰት ተደርጓል ብለዋል።

የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊና የእንስሳት ዘርፍ አስተባባሪ አቶ ቶሌራ ደበላ በበኩላቸው፤ እንደ አጠቃላይ በክልሉ ከ2013 ጀምሮ በአራት ዞኖች የመኖ ልማት ኢንሼቲቭ ተቀርጾ እየተሰራ ነው ብለዋል። ስድስት ሚሊዮን ሄክታር ላይ የከብቶች የተለያዩ መኖ ዓይነቶች እየለማ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።

በተጨማሪም በዚህ በጀት ዓመት ብቻ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር ላይ የከብቶች ግጦሽ ማሻሻያ ተደርጓል ብለዋል።

በደጋማና ቆላማ አካባቢዎች የሚበቅሉ የሳር ዝርያዎች በመለየት ከሰባት ሺህ ኩንታል በላይ ዘር ማቅረብ መቻሉን ጠቅሰው፤ በቀጣይም የተዘራው መኖ በወቅቱ ተሰብስቦ ወደ መጋዘን እንዲገባ የሳር ማጨጃ ማሽን ተገዝቶ መግባቱን ተናግረዋል።

እንደ አቶ ቶሌራ ገለጻ፤ ከዚህ በፊት ያጋጠመው የድርቅ ችግር አሁንም በከብቶች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ በርካታ ቁጥር ያላቸው የመኖ ባንኮች ተገንብተው መኖ እየተከማቸ ይገኛል።

በሚቀጥለው በጀት ዓመትም በክልሉ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በእንስሳት መኖ እንዲለማ አቅጣጫ መቀመጡንም ነው አቶ ቶሌራ ያብራሩት።

በዞኑ ከዚህ በፊት ያጋጠመው ድርቅ ተቋቁሞ ውጤት ከማምጣት በተጨማሪ ከአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ መኖ እየለማ ነው ያሉት ደግሞ የቦረና ዞን ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጃለላ ዱለቻ ናቸው።

ማዕከሉ የከብቶች ዝርያ እንዳይጠፉ የሚያስፈልገውን ግብዓት አሟልቶ እየሰራ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በቀጣይ ዝርያዎቹን ለአርብቶ አደሩ ለማከፋፈል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

# በተጎዱ አካባቢዎች ላሉ ሕፃናት ተደራሽ የትምህርት ሥርዓት ለመፍጠር ያለመ ኮንፍረንስ ተካሄደ

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በተጎዱ አካባቢዎች ላሉ ሕፃናት ተደራሽ የትምህርት ሥርዓት ለመፍጠር የሚያስችል ዓለም አቀፍ የምርምር ኮንፍረንስ በኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ አዘጋጅነት ተካሄደ፡፡

የኮተቤ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ብርሀነመስቀል ጠና (ዶ/ር) በመድረኩ ላይ እንደገለጹት፤ "የድንገተኛ ጊዜ ትምህርት እና በችግር በተጎዱ አካባቢዎች ላሉ ሕፃናት በጨዋታ ላይ የተመሰረተ የመማር አቀራረቦች" በሚል መሪ ሃሳብ የሚካሄደው ዓለም አቀፍ የምርምር ኮንፍረንስ በተጎዱ አካባቢዎች ላሉ ሕፃናት ተደራሽ የትምህርት ሥርዓት ለመፍጠር ያስችላል፡፡

በዓለም ብሎም በሀገሪቱ በተለያዩ ምክንያቶች ሰፊ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተፈናቀሉ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህም በአደጋ አካባቢዎች ላይ የሚገኙ ሕፃናት ከትምህርት ገበታ ውጪ የሚሆኑበት እና የአዕምሮ ሕመም ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ የሚፈጥር ነው፡፡

በመሆኑም መድረኩ በጦርነት አካባቢ የሚገኙ ሕፃናት ከትምህርት ውጪ የሚሆኑበትን ሁኔታ በማስቀረት ተደራሽ የትምህርት ሥርዓት ለመፍጠር እንዲሁም በጨዋታ የትምህርት ሥርዓት በመጠቀም የሕፃናቱን አዕምሮ ወደቀድሞ ለመመለስ ያለመ ነው ብለዋል።

ለዚህም የጸጥታ ችግር አካባቢ የሚገኙ መምህራን አጫጭር ስልጠና የመስጠት ሥራ እንደሚሠራ ገልጸው፤ የዘርፉን ችግር ለመፍታትም የትምህርት ካሪኩለም በመቅረጽ የድንገተኛ ጊዜ ትምህርት በማስተርስ ዲግሪ ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ ለመጀመር እቅድ መያዙን አስታውቀዋል፡፡



ብርሀነመስቀል ጠና (ዶ/ር)



አቶ ኮራ ቶሹኔ

በትምህርት ሚኒስትር የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ኮራ ቶሹኔ በበኩላቸው፤ ኮንፍረንሱ በጸጥታ ችግር ምክንያት የተደራጀ የትምህርት ሥርዓት እና የትምህርት እድል የተዛባባቸው አካባቢዎች ላይ እንዴት ማስተካከል እንደሚቻል የሚያመላክትና ያሉበትን ሁኔታ በማገናዘብ ትምህርት ለመስጠት የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ከማስተማር ባለፈ የጨዋታ ትምህርት ሥርዓት በመፍጠር ሕፃናት ከደረሰባቸው የሥነልቦና እና አካል ጉዳት እንዲያገግሙ ይረዳል ሲሉ አቶ ኮራ ተናግረዋል፡፡

በኮንፍረንሱ የሚቀርቡ ምርምሮች የተፈናቃዮችን ችግር ቀረብ ብሎ ለማየትና ለመለየት፣ ለፖሊሲ እና ሕግ ግብአት ለማግኘት እንዲሁም የጥናቱን ውጤት ለሚመለከተው አካል ይፋ በማድረግ ለስደተኞች የሚሰጠው አገልግሎት እንዲሻሻልና የስደተኞች ጉዳይ መመሪያ ፖሊሲ ለማውጣት ያስችላል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ኮንፍረንሱ የኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ከኢፌዴሪ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከፕለይማተርስ ኢትዮጵያ የተዘጋጀ የምርምር ኮንፍረንስ ሲሆን፤ ከሀገር ውስጥና ከውጭ የተወጣጡ ባለድርሻ አካላት ተሳትፈውበታል፡፡

# በስምጥ ሸለቆ በሚደረገው የማይክሮ አልጌ ልማት የግል አልሚዎች እንዲሳተፉ ጥሪ ቀረበ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዳሚ ቱሉ፡- በስምጥ ሸለቆ በሚደረገው የማይክሮአልጌ ልማት የግል አልሚዎች እንዲሳተፉ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጥሪ አቀረበ።

ከስምንት ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገበትና በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነውን የማይክሮ አልጌ የምርምር ማእከል ትናንት ተመርቋል።

በምርቃት ሥነሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ባይሳ በዳዳ እንደገለጹት፣ ስምጥ ሸለቆ ለማይክሮ አልጌ ምርት አመቺ በመሆኑ ከመንግሥት ባለፈ የግል አልሚዎች በሥራው ሊሳተፉ ይገባል።

መንግሥት ዘርፉ እንዲያድግ በትኩረት እየሠራ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ማይክሮ አልጌን እንደ ምግብነት በመጠቀም በሽታን የመከላከል አቅምን ከማሳደግ ባለፈ ማይክሮ አልጌን አሠራር ግልጽ ለማድረግና አልሚዎች በስፋት እንዲሰማሩ የፖሊሲ ማሻሻያዎች እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

ማይክሮ አልጌን በስፋት በማምረት ከሀገር ውስጥ ፍጆታ ባለፈ ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ እንደሚገባ አስታውቀዋል።

አሁን ላይ ማይክሮ አልጌ በሀገራችን የተለመደ የምግብ አይነት አይደለም ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ወደፊት በስፋት የማምረትና የማስተዋወቅ ሥራ እንደሚሠራ ገልጸዋል።

ማይክሮ አልጌ ከየትኛውም የምግብ አይነት ጋር ቀላቅሎና በፈሳሽ መልክ መጠቀም የሚቻል ሲሆን፤ በኢትዮጵያ የሚስተዋለውን የመቀንጨር ችግር ለመቅረፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ብለዋል።

የማይክሮ አልጌ የምርምር ማእከል እውን እንዲሆን ከስድስት ዓመት በላይ ጥረት ሲደረግ እንደነበር አስታውሰው፤ በቀጣይም ማእከሉ ለሀገር ኢኮኖሚ ተጨማሪ ገቢ እንዲያመጣ በቅንጅት በመሥራት ግንዛቤን የማሳደግ ሥራ ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ሀገር የተያዘ የእድገት እቅድን ለማሳካት በቅንጅት ከመሥራት ባለፈ በቴክኖሎጂ የተመሠረተ ሥራ መሥራት ተገቢ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ፕሮፌሰር ካሳሁን ተስፋዬ በበኩላቸው እንደገለጹት፣ የማይክሮ አልጌ የምርምር ማእከል በአንድ ሺህ ሁለት መቶ ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን፤ ከስምንት ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ወጥቶበታል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ካሰበችው የኢኮኖሚ እድገት ለመድረስ የዜጐችን ደህንነት መጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ ኢንስቲትዩቱ ችግር ፈች የምርምር ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። በተለይ ኢትዮጵያ በስምጥ ሸለቆ ያላትን የማይክሮ አልጌ ምርትን በመጠቀም የመቀንጨር ችግርን ለመቀነስ እየሠራች ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የመቀንጨር ምጣኔን ለመቀነስ የሰቆጣ ቃልኪዳንን ተግባራዊ በማድረግ ለውጦች እየተመዘገቡ ነው። ውጤቱን ለማስቀጠል ኢንስቲትዩቱ ከኦሮሚያ ግብርና ምርምር ማእከል ጋር በመተባበር የማይክሮ አልጌ የምርምር ማእከልን መገንባቱን ገልጸዋል።

የማይክሮ አልጌ (ስፓይሩሊና) ምርምርና ልማት ማዕከልን የባዮና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትና አዳሚ ቱሉ የስፓይሩሊና ምርምርና ማምረቻ ማእከል ከኦሮሚያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር አስመርቀዋል።



አቶ ተስፋዬ በልጅጌ

# በመሬትና ሕንፃ ላይ ታክስ ለመሰብሰብ የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ ለምክር ቤት ቀረበ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ:- በከተማ ውስጥ በሚገኝ መሬት እና በሕንፃ ላይ የንብረት ታክስ እንዲሰበሰብ የሚያስችል የፌዴራል የንብረት ታክስ ረቂቅ አዋጅ ለምክር ቤት ቀርቦ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ተመራ።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት ባካሄደው 3ኛ ዓመት 33ኛ መደበኛ ስብሰባው፤ የፌዴራል የንብረት ታክስ ረቂቅ አዋጅን በሦስት ተቃውሞ በአብላጫ ድምጽ ለፕላን በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቷል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ በልጅጌ ስለአዋጁ ባቀረቡት አጭር ማብራሪያ እንደተናገሩት፤ ከመሬት ጋር ከተያያዘ ንብረት መንግሥት የሚያገኘው ገቢ እጅግ በጣም አነስተኛ በመሆኑ በመሬትና በሕንፃ ላይ ዋጋን መሠረት ያደረገ ዘመናዊ የንብረት ታክስ መጣል አስፈላጊና ወቅታዊ ነው።

በከተሞች ውስጥ ከሚገኘው ሀብት ውስጥ እያደገ የመጣውን የመንግሥት የወጪ ፍላጎት በተወሰነ ደረጃ ለመሸፈን የሚያስችል የተሻለ ሀብት ማሰባሰብ እንዲቻል ዘመናዊ የንብረት ታክስ ሥርዓት መዘርጋት እንደሚገባም ነው የጠቆሙት።

በረቂቅ አዋጁ ነጻ እንዲሆኑ የተቀመጡት፤ የሃይማኖት ተቋማት ለአምልኮ ተግባር እንዲሁም ለመካነ መቃብር አገልግሎት የሚጠቀሙበት ቦታና ቤት እንዲሁም በከተማ ውስጥ ያለ ሙሉ ለሙሉ ለግብርና ሥራ የዋለ መሬት ከታክሱ ነጻ እንዲሆን ቀርቧል።

በገንዘብ ሚኒስቴር በዝርዝር ተለይተው ከታክሱ ነጻ እንዲሆኑ የተደረጉ የፌዴራል መንግሥት አካላት፣ ለሕዝብ ጥቅም የሚሰጡ ንብረቶች እና በሁለትዮሽ ወይም በይነ መንግሥታዊ ስምምነት የተቋቋሙ ተቋማት ነጻ እንዲሆኑ የተደረጉ ድርጅቶች ናቸው።

በአብዛኞቹ የዓለም ሀገራት በከተማና በገጠር በሚገኝ መሬት ላይ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ‹‹የመሬት ታክስ›› በሚል ስያሜ ሲሰበሰብ መቆየቱን አስታውሰው፤ በኢትዮጵያም ከ1937 ዓ.ም ጀምሮ ከንብረት ላይ በተለያዩ መጠሪያዎች መጠነኛ ክፍያ በመሰብሰብ ላይ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ረቂቅ አዋጅ እና የአካባቢና ማህበራዊ ተጽእኖ ግምገማ ረቂቅ አዋጅ፣ የአረንጓዴ አሻራ እና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድን ማቋቋሚያና አስተዳደር ረቂቅ አዋጅንም መርምሮ ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች መርቷል።

በኢትዮጵያ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ለሁለተኛው የከተሞች የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል የ275 ሚሊዮን ዶላር የብድር ስምምነት አዋጅን በሙሉ ድምጽ አፅድቋል።

# በመዲናዋ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ዜጎች የበጎ ፍቃድ መርሀ ግብሩ ተጠቃሚ ይሆናሉ

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- 2016/17 የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሀ ግብር በመዲናዋ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ዜጎች ተጠቃሚ ይሆናሉ ሲል የአዲስ አበባ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የ2016/17 የክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ማስጀመሪያ መርሀ ግብር ‹‹በጎ ፍቃድ ለማህበራዊ ለውጥ›› በሚል መሪ ሃሳብ በትናንትናው ዕለት አካሂዷል፡፡

በመርሀ ግብሩ ተገኝተው መክፈቻ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ የብልጽግና ፓርቲ ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ አለማየሁ እጅጉ፤ በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሀ ግብር የተቸገሩ ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ በቅድሚያ በትክክል በችግር ያሉትንና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን መለየት አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

በመዲናዋ በርካታ ኑሮ ከአቅም በላይ የሆነባቸው ዜጎች አሉ፤ ኑሮ ከአቅም በላይ የሆነባቸውን ዜጎች በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ከችግራቸው ማውጣት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የተቸገሩትን ብቻ መርዳት ሳይሆን መሥራት የሚችሉትን አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ልማታዊ ኃይል ማድረግ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ አለማየሁ ገለጻ፤ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የተቸገሩ ዜጎችን ተጠቃሚ በማድረግ ልማትን በማፋጠን ደረጃ ትልቅ ውጤት እያስገኘ ነው፡፡ የተቸገሩ ዜጎችን ለመርዳት የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል፡፡



አቶ አለማየሁ እጅጉ፤



ወይዘሮ ወይንሸት ዘሪሁን

የአዲስ አበባ ከተማ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ወይንሸት ዘሪሁን በበኩላቸው፤ በ2016/17 ዓመት በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት በተለያየ ችግር ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ነው።

በክረምት በበጎ ፈቃድ አገልግሎት በመዲናዋ የሚገኙ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዜጎችን በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ ዘርፍ ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን፣ የግል ባለሀብቶችን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማሳተፍ ለሀገር ውለታ የዋሉና ለችግር የተጋለጡ ዜጎችን ለመርዳት በትኩረት እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በከተማ ግብርና፣ የቤት እድሳትና ግንባታ፣ በደም ልገሳ፣ የጎርፍ አደጋ የመከላከል፣ አቅም ለሌላቸው ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ የማሟላት፣ ምገባና የተለያዩ ድጋፎች የማድረግ ሥራ እንደሚከናወን ጠቁመዋል።



# ወደ ውጭ በሚላኩ የግብርና ምርቶች ላይ ዘመናዊ የቁጥጥርና ደህንነት ሥርዓት እየተገነባ ነው

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ወደ ውጭ በሚላኩ የግብርና ምርቶች ላይ ዘመናዊ የቁጥጥርና ደህንነት ሥርዓት እየተገነባ መሆኑን የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር አምራችና ላኪዎች ማህበር እና በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የተዘጋጀው የግብርና ውጤቶች ቁጥጥርና ደህንነት ላይ ያተኮረ ጉባኤ ትናንት ተካሂዷል፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ድሪባ ኩማ በወቅቱ ባደረጉት ንግግር፤ ባለስልጣኑ ወደ ውጪ የሚላኩና ከውጭ ወደ ሀገር ቤት የሚገቡ የግብርና ምርቶችን የደህንነትና ቁጥጥር አገልግሎት እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡

እስካሁን የነበረው የአገልግሎት አሰጣጥ በአብዛኛው ወረቀት ላይ የተመሰረተ እንደሆነና አሁን ላይ አገልግሎቱን ወደ ዲጂታል ሥርዓት ለመቀየር ከአውሮፓ ኅብረትና ከትሬድ ማርክ አፍሪካ ጋር እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ከ80 በመቶ በላይ ወደ ውጭ የምትልከው በአብዛኛው ግብርና ምርት ነው ያሉት አምባሳደር ዲሪባ፣ አብዛኛው የውጭ ምንዛሪ ገቢም ከግብርና ምርቶች እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

እንደ አምባሳደር ድሪባ ገለጻ፣ የግብርና ምርቶች ጤናቸውንና ጥራታቸውን የሚቆጣጠረው ባለስልጣኑ ነው፡፡ ምርቶቹ ደህንነታቸውና ጥራታቸው የተጠበቀ እንዲሁም የተቀባይ ሀገራትን መስፈርት ያሟሉ መሆናቸውም ይረጋገጣል።

ይህንን ለማሳካት በወረቀት ሰርቲፊኬት የሚሰጠው ማረጋገጫ በብዙ ሀገራት ተቀባይነት እያጣ ስለመጣና አገልግሎት ላይም ጫና በመፍጠሩ በአሁኑ ወቅት አገልግሎቱን ሙሉ በሙሉ ወደ ኤሌክትሮኒክስ የመቀየር ሥራ እየተሠራ እንዳለ አስታውቀዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በአየር ለውጥ ምክንያት እጽዋትን የሚያጠፉ በርካታ ተባዮች፣ በሽታዎችና ባክቴሪያዎች፣ እየተፈጠሩ እንዳሉ፤ በዚህም ምክንያት የአውሮፓ ኅብረትና ሌሎችም የኢትዮጵያን ምርት የሚቀበሉ ሀገራት የቁጥጥር ሥርዓታቸውን በየጊዜው እየቀየሩ መሆናቸውን አንስተዋል።

ከቁጥጥር ሥርዓቱ መጥበቅ ጋር ተያይዞ ኢትዮጵያም እነዚህ አካላት ከሚያወጡት የቁጥጥር ሥርዓት ጋር የሚመጣጠን ሥርዓት መገንባት ካልቻለች ምርቶች ላይ አሉታዊ ጫና ስለሚፈጥር የዘመነ የምርት የቁጥጥርና ደህንነት ሥርዓት እየተገነባ እንዳለ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ወንዳለ ሀብታሙ በበኩላቸው፤ ጠንካራ ሀገራዊ የዕፅዋት ንፅህና አጠባበቅ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ ትብብር አስፈላጊ መሆኑን አጽንኦት ሰጥተዋል። የሥርዓቱን ስኬትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉም ጠይቀዋል።

አቶ ወንዳለ አክለውም፤ የዕፅዋት ሀብቶችን በመጠበቅ ረገድ ቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ ማተኮር፤ በዚህም የገበያ ተደራሽነትን ለመጠበቅና ለማስፋት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚወጡትን መስፈርቶች ማክበር አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ አበባ ተክልና ፍራፍሬ አምራችና ላኪዎች ማህበር ዋና ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ ዘውዴ፤ ዓለም አቀፍ የእጽዋት ጤና ደረጃዎችን ለማስጠበቅ ከተቆጣጣሪ አካላት፣ ከግሉ ሴክተርና ከተለያዩ አካላት ጋር ተቀራርቦ መሥራት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

# ኤጀንሲው ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ የኩነት መረጃዎችን ዲጂታላይዝድ አድርጓል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ በወረቀት የነበሩ የኩነት መረጃዎችን ዲጂታላይዝድ ማድረጉን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ የአይሲቲ ዳይሬክተር አቶ አዕምሮ ካሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኤጀንሲው ካለፈው ዓመት ጀምሮ የወረቀት መረጃዎችን ዲጂታላይዝ የማድረግ ሥራ እየሠራ ነው።

በዚህም ከ1935 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2001 ያለውን የኩነት መረጃ ዲጂታላይዝድ የማድረግ ሥራ በማዕከልና በክፍለ ከተሞች እየተሠራ ነው ያሉት አቶ አዕምሮ፤ በወረቀት የነበሩ የኩነት መረጃዎችን ዲጂታል የማድረግ ሥራ ከተጀመረ ጀምሮ ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ መረጃዎችን ዲጂታል ማድረግ መቻሉን አስታውቀዋል።

በ2016 በጀት ዓመት በወረቀት የነበሩ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የኩነት መረጃዎችን ዲጂታል ለማድረግ ታቅዶ እስካሁን ከ800 ሺህ በላይ መረጃዎች ዲጂታላይዝ በማድረግ የእቅዱን 56 በመቶ ማሳካት መቻሉን ገልጸዋል።

የግብዓት አቅርቦት እጥረት፣ በቂ የሰው ኃይል አለመኖር እና ሌሎች ምክንያቶች የእቅዱ አፈጻጸም ደካማ እንዲሆን ምክንያት መሆናቸውን አንስተዋል።

የኩነት መረጃዎችን ዲጂታል የማድረግ ሥራው በማዕከል ደረጃ በ2015 ዓ.ም በክፍለ ከተማ ደረጃ ደግሞ በተያዘው የ2016 በጀት ዓመት የተጀመረ መሆኑን ጠቅሰው፤ እስከ 2001 ዓ.ም ያሉ የወረቀት ኩነት መረጃዎችን እስከ 2017 ዓ.ም መጨረሻ ዲጂታላይዝ አድርጎ ለማጠናቀቅ እየተሠራ ነው ብለዋል።

አሁን ላይ ዲጂታል የማድረግ ሥራው በማዕከልና በሁሉም ክፍለ ከተማዎች እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ዲጂታል ለማድረግ የታቀደው አጠቃላይ የኩነት መረጃ ሰባት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጋ መሆኑን ተናግረዋል።

ወደ ዲጂታል እየተቀየሩ ያሉት መረጃዎች የልደት፣ የፍቺ፣ የጋብቻ፣ የሞት እና ሌሎች ደጋፊ መረጃዎች መሆናቸውን አስታውቀዋል።

መረጃዎች ዲጂታል መደረጋቸው የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን ለማዘመን የሚረዳ መሆኑን የጠቀሱት አቶ አዕምሮ፤ በተጨማሪም የኩነት መረጃዎቹ ዲጂታል መሆን የመረጃ ደህንነትን ለማስጠበቅ፣ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሳለጥ፣ ጊዜና ቦታን ለመቆጠብ፣ የሥራ ባህልን ለማዳበር እና ሌሎች ጠቀሜታዎች እንዳሉት አስረድተዋል።

ተቋሙ አሠራርን ማዘመን ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ መሆኑን ተረድቶ መረጃዎችን ዲጂታላይዝድ የማድረግ ሥራውን በትኩረት እየሠራበት መሆኑንም ጠቁመዋል።

# ከዓለም አቀፍ ባለሀብቶች በተለየ ለሀገር ውስጥ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

መድረክ በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ትናንት ተካሂዷል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አክሊሉ ታደሰ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ሀገራዊ የኢንቨስትመንትና የኢኮኖሚ ሪፎርሙን መሠረት በማድረግ የተተገበሩ የሪፎርም ሥራዎች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ያለውን የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ተሳትፎ አሳድገዋል፡፡

በዚህም በአሥራ ሦስት ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከሚገኙ ኢንቨስተሮች 55 በመቶው የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል ያሉት አቶ አክሊሉ፤ አሁን ላይ ከዓለም አቀፍ ባለሀብቶች በተለየ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ልዩ እድል መዘጋጀቱን ገልጸዋል።

በኮርፖሬሽኑ ከተደረጉ የሪፎርም ሥራዎች መካከልም የሊዝ ቅድመ-ክፍያ ከአሥር በመቶ ወደ አምስት በመቶ እንዲሁም ከሼድ ኪራይ በፊት ከነበረበት 10 በመቶ ቅናሽ መደረጉን ለአብነት ጠቅሰዋል፡፡

በዚህም ካለፈው ሁለት ዓመት ወዲህ ከ60 በላይ ሀገር በቀል ባለሀብቶች የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመው ወደ ሥራ መግባታቸውን ተናግረዋል።

ከሁለት ዓመት በፊት በአሥራ ሦስት ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ከሚገኙ ኢንቨስተሮች የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ድርሻ አስር በመቶ እንደነበር ያነሱት አቶ አክሊሉ፤ አሁን ግን የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች 55 በመቶ ሆኗል። ለዚህም መንግሥት በርካታ ሥራዎችን ሠርቷል። አሁንም የተለያዩ ማሻሻያዎች ተደርገዋል ነው ያሉት።

ከዚህም ውስጥ የታሪፍ ማሻሻያ፣ የ40 ዓመት ውል፣ የለማ መሬት፣ የገበያ ትስስር እና ሌሎች የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ማሻሻያዎች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ መንግሥት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ልዩ ትኩረት የሰጠ በመሆኑ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ኢንቨስት እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

መድረኩ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሃሳብ አመንጭነት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን አቅም ለማሳደግ እና አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች በስታርትአፕ እንዲጀመሩ በተሰጠ አቅጣጫ መሠረት የተዘጋጀ መሆኑ ተገልጿል። በዚህም መድረኩ ለሀገር በቀል ኩባንያዎች ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ተብሎ እንደሚጠበቅ ተገልጿል።

# ቴክኒክና ሙያ - የኢኮኖሚ ዕድገት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ላይ እንዲከፈት መደረጉን ይናገራሉ። ከትምህርት ቤቱ መቋቋም በኋላ በአንጻራዊነት የቴክኒክና ሙያ አስፈላጊነት ላይ መጠነኛ የአመለካከት ለውጥ መምጣቱንም ያስረዳሉ። ይህም ቢሆን ግን በሚፈለገው ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶት በማኅበረሰቡ ዘንድ እውቅና ተሰጥቶት እንዲያድግ እንዳልተደረገ ነው የሚያስገነዝቡት።

ከ1986 በኋላ በተለይም ከ1994 ወዲህ አዲስ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ተዘጋጅቶ የስልጠና ዘርፉ ሥርዓት ተዘርግቶለት መሰጠት መጀመሩን አንስተው፤ እስካሁን ድረስ አጥጋቢም ባይሆን ዘርፉ በተሻለ ትኩረት እያገኘ የአመለካከት ለውጥም እየመጣ እንደሚገኝ ይጠቅሳሉ።

ባለንበት ሥርዓት ደግሞ መንግሥት የዘርፉን ቁልፍ ሚና ተገንዝቦ በቅርበት የሚያስተባብረውን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ማቋቋሙን ያነሱት ብሩክ (ዶ/ር)፤ ይህም ካለፉት ጊዜያት በተሻለ ዘርፉ የበለጠ ትኩረት እንዲያገኝ እንዳገዘው ይናገራሉ።

ዳይሬክተሩ እንደሚሉት፤ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መቋቋም በተጨማሪ፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሲከፈቱ የአካባቢያቸውን ጸጋና ገበያ ማዕከል አድርገው እንዲከፈቱ የሚያስችል እሳቤን ተግባራዊ ማድረግ ተጀምሯል። ከመሥሪያ ቤቱ መቋቋም በኋላ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲም ወጥቷል። እነዚህን አዳዲስ እሳቤዎችና ጅምር ጥረቶች የበለጠ እያጠናከሩ መሄድ ያሻል።

ዘርፉ ያለበት ከፍተኛ ተግዳሮት ማኅበረሰቡ ለቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ያለው ተገቢ ያልሆነ አመለካከት መሆኑንም የሚያነሱት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር፣ ይህንን ሁኔታ ለመቀየር ሰፊ የምስል ግንባታ ሥራ መሥራት ይጠበቃል። ዘርፉ ሰዎች ምርጫ አጥተው ሳይሆን ፍላጎት ኖሯቸውና ራሳቸው መርጠው የሚገቡበት ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ ያስረዳሉ።

ዛሬም ድረስ ወላጆች ልጆቻቸው ወደ ዩኒቨርሲቲ እንጂ ወደ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሲገቡ ደስተኛ እንደማይሆኑ ያነሱት ዳይሬክተሩ፤ ማኅበረሰቡ "ቴክኒክና ሙያ ሕይወት ይቀይራል፣ ተግባራዊ ስልጠና ያስገኛል፣ ወደ ሥራ መግባት ያስችላል" የሚል እምነትን እንዲያዳብር ትልቅ ሥራ እንደሚጠበቅ ነው የተናገሩት።

ቴክኒክና ሙያ ስልጠና በማንኛቸውም መስክ መደበኛና መደበኛ ባልሆነ መልኩ ሊሰጥ የሚችል ስልጠና መሆኑን ያነሱት ደግሞ፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራና ክህሎት ቢሮ በምክትል ቢሮ ኃላፊ ደረጃ የቢሮ ኃላፊ አማካሪ አቶ ቸርነት በላቸው ናቸው። እርሳቸው እንዳሉት ስልጠናው በርካቶችን ሊያሳትፍ የሚችልና ልክ እንደ ቀለም ትምህርት ሁሉ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ላይ መድረስም የሚያስችል ነው።

በሀገራችን ካለፉት ጊዜያት አንስቶ ለሙያ ስልጠና ትኩረት ሲሰጥ እንዳልነበር የሚያነሱት አቶ ቸርነት፤ የሙያው ውጤት ቢፈለግም ለባለሙያው የሚሰጠው ቦታና ክብር ግን አናሳ ነው። ባለሙያውን ዝቅ አድርጎ የማየት ለረጅም ጊዜ የቆየ የአመለካከት ችግር መኖሩ ባለሙያው ሙያውን ሳይንሳዊ በሆነና በተሻለ መንገድ እንዳያሳድግ ማነቆ ሆኖበት እንደቆየ ይጠቁማሉ።

የኢንዱስትሪዎች ተወዳዳሪነት የሚወሰነው ብቃት ባለው የሰው ኃይል ነው ያሉት አቶ ቸርነት፤ ዘርፉ ያሉበትን ፈተናዎች ማለፍ፣ የአመለካከት ችግሮችንም መቅረፍ ከቻለ የኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ፤ ከውጪ የምናስገባቸውን ምርቶች በራሳችን የማምረት አቅም ለመተካትና ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ሚና ለመጫወት ይረዳል ሲሉ ነው የሚያስረዱት።

በአዲስ አበባ ሥራና ክህሎት ቢሮ የውጤት ተኮር ትምህርትና ስልጠና ሱፐርቫይዘር አቶ ታደለ አየነውም ዜጎች መሥራትና መለወጥ ካለባቸው የግድ ሙያ ባለቤት መሆን አለባቸው ይላሉ። የቴክኒክና ሙያ ዜጎች በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ተቀጥረውም ሆነ በራሳቸው ሥራ ፈጥረው ራሳቸውን፣ ቤተሰባቸውንና አካባቢያቸውን መቀየር የሚችሉበትን ሙያ የሚጎናጸፉበት የስልጠና ዘርፍ እንደሆነም ያብራራሉ።

በየጊዜው እየጨመረ ለመጣው የኢንዱስትሪዎች መስፋፋትና የሰው ኃይል ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት የስልጠና ዘርፉን ማጠናከር የግድ አስፈላጊ እንደሆነም ያስረዳሉ።

አቶ ታደለ እንደሚሉት፤ ቴክኒክና ሙያ ኢንዱስትሪዎቻችን ምርታማነታቸው እንዲያድግ፣ ተወዳዳሪነታቸው እንዲጨምር በአመለካከቱም ሆነ በክህሎት የበቃ የሰው ኃይል የማቅረብ ሚና ያለው ትልቅ ዘርፍ ነው። ይህንን ማዕከል አድርገው በተሰሩ ሥራዎች ዘርፉ ላይ ያለው ተገቢ ያልሆነ አመለካከት በመጠኑም ቢሆን እየተቀረፈ መጥቷል።

የሚፈለገውን ያህል ባይሆንም ዩኒቨርሲቲ መግባት የሚያስችል ውጤት ያላቸው ዜጎች በፍላጎታቸው ወደ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት እየገቡ መሆኑን ጠቁመው፤ በአጭር ጊዜ የሙያ ባለቤት፣ የሥራ ባለቤት እሆናለሁ የሚለው አመለካከት እየተፈጠረ ይገኛል ሲሉ ያስረዳሉ።

ዘርፉን በመደገፍ ረገድ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስልጠና ተቋማቱን በበጀት እየደገፋቸው መሆኑን በማንሳት፤ በአሁኑ ወቅት ለቴክኒክና ሙያ የተሰጠው ትኩረት ተጠናክሮ ከቀጠለና የአመለካከት ለውጡ ላይም የበለጠ ከተሠራ ዘርፉ በሀገር እድገት ላይ መጫወት የሚገባውን ሚና በሚገባ የመወጣት እድል ይኖረዋል ሲሉ ያስረዳሉ።

# ኢትዮጵያ በብሪክስ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ኢትዮጵያ በሩሲያ በተካሄደው የብሪክስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች መድረክ ላይ በአምባሳደር ታዬ አፅቀሥላሴ በተመራ ከፍተኛ የልዑካን ቡድን አማካኝነትና የብሔራዊ ተወካዮች መድረክ ላይ በብሔራዊ ባንክ ገዢ በአቶ ማሞ ምህረቱ በተመራ የልዑካን ቡድን ተሳትፋለች።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ነብዩ ተድላ ለጋዜጠኞች በሰጡት ሳምንታዊ መግለጫ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በብሪክስ ማዕቀፍ ውስጥ ንቁ ተዋናይ እየሆኑ ከመጡ ሀገራት መካከል አንዷ ሆናለች ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በብሪክስ የስብሰባ መድረኮች ላይ ያደረገችው ንቁ ተሳትፎ ብሪክስን በትክክለኛው ወቅት መቀላቀሏን በድጋሚ ያረጋገጠ ክስተት መሆኑን በመግለጽ፤ በብሪክስ ማዕቀፍ ውስጥ ንቁ ተዋናይ እየሆኑ ከመጡ ሀገራት መካከል አንዷ መሆኗን ተናግረዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ፤ ከብሪክስ የስብሰባ መድረኮች በተጓዳኝ ከስምንት የብሪክስና የተጋባዥ ሀገሮች ጋር ተወያይተዋል ያሉት አምባሳደሩ፤ ከቻይና፣ ብራዚል፣ ደቡብ አፍሪካና ሩሲያ ጋር የተናጥል ውይይቶች መደረጋቸውን ተናግረዋል፡፡

ሀገራቱ ኢትዮጵያ የብሪክስ አዲሱ ልማት ባንክ አባል ለመሆን ያቀረበችው ጥያቄ እንዲፋጠን ድጋፍ እንደሚያደርጉ ማረጋገጣቸውን ጠቅሰው፤ በአዳዲስ የትብብር መስኮች ላይ መተባበር የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች መፈጠራቸውንም ገልጸዋል፡፡

እንደ አምባሳደር ታዬ ገለጻ፤ በብሪክስ አባል ሀገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያ በብሪክስ ተሳትፎዋ ያላትን ሚና ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ አንኳር ርምጃዎች ወስዳለች፡፡ አባል ሀገራቱ ብሪክስ በወቅታዊና አንገብጋቢ ዓለምአቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ያለውን ገንቢ ሚና እንዲያሳድግም ጥሪ አስተላልፈዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፋይናንስና የጸጥታ ተቋማት የታዳጊ ሀገራትን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ ማሻሻያ እንደሚያስፈልጋቸው መግለጻቸውን ጠቁመው፤ ኢትዮጵያ ውጤታማ የባለብዙ ወገን ግንኙነትን በጋራ ለማስፈን ያላትን ቁርጠኝነት ማረጋገጣቸውንም ተናግረዋል፡፡

በስብሰባው ማጠናቀቂያ የጋራ መግለጫ፤ የኢትዮጵያን ጥቅምና ፍላጎት ያስጠበቀ እንዲሆን መደረጉን ገልጸው፤ ኢትዮጵያን ጨምሮ አዳዲስ አባላት በብሪክስ ውስጥ በተሳለጠ መልኩ ወደ ማዕቀፉ እንዲገቡ ድጋፍ እንዲደረግ መግባባት ላይ መደረሱን ጠቁመዋል፡፡

የዓለም አቀፉ የፋይናንስ ተቋማት ማሻሻያ የሀገራትን ወቅታዊ የኢኮኖሚ ደረጃ የዋጀ እንዲሆን መስማማታቸውን ጠቁመው፤ የጸጥታው ምክር ቤት ዲሞክራሲያዊ አካታችና ውጤታማ ለማድረግ የሚከናወነው ማሻሻያ የአፍሪካን ፍላጎት ያማከለ እንዲሆን መግባባት ላይ መደረሱን አስረድተዋል፡፡

በሌላ በኩል በዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ዙሪያ አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ከተ.መ.ድ 78ኛው ጠቅላላ ጉባዔ ፕሬዚዳንት ጋር ተወያይተዋል፡፡ በዚህም ተ.መ.ድ ለኢትዮጵያ የሰላምና የልማት ጥረቶች ድጋፉን እንደሚያጠናክር ማረጋገጣቸውንም ገልጸዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ ከፊንላንድ የውጭ ንግድና ልማት ሚኒስትር ጋር የሁለትዮሽ የኢኮኖሚ ትብብር ለማጠናከርና በቅርቡ የፖለቲካ ምክክር ለማድረግም መስማማታቸውን አውስተዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው ከእንግሊዝ የአፍሪካ ቀንድና ቀይ ባህር ልዩ ልዑክ አሊሰን ብላክበርን ጋር ባደረጉት ውይይት፤ በቀጣናው ሰላምና መረጋጋት ለማምጣትና የጋራ ጥረቶችን ለማሳደግ ከመግባባት ላይ መደረሱን ቃል አቀባዩ ገልጸዋል።

# ለዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ ሰባት ነጥብ ስድስት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ችግኞች መካከል 56 በመቶ የሚሆኑት ብዝሀ ጥቅም ያላቸው የፍራፍሬና የማገዶ ችግኞች ሲሆኑ፤ 44 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ የአካባቢ ጥበቃና የደን ሽፋንን የሚጨምሩ ችግኞች መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ የተዘጋጁትን ችግኞች ለመትከል አንድ ነጥብ ስምንት ሄክታር መሬት ለመለየት ታቅዶ እስከሁን አንድ ነጥብ 71 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ተለይቷል፡፡ ከተለየው መሬት ውስጥ 950 ሺህ ሄክታሩ ካርታ የተዘጋጀለትና ማንም በየትኛውም አካባቢ ሆኖ ችግኞችን መከታተል የሚያስችል ሁኔታ መፈጠሩን ተናግረዋል፡፡

ከችግኝ ዝግጅትና መሬት ልየታ በተጨማሪ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች አምስት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ጉድጓዶች መዘጋጀታቸውን አስታውቀዋል፡፡

በዛሬው ዕለት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተገኙበት የ2016/17 የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር የቅድመ ማስጀመሪያ ፕሮግራም የሚከናወን ሲሆን፤ በአምስት ዓመት በተተከሉት ችግኞች ከምግብ ዋስትና፣ ከአካባቢ ጥበቃ፣ ከደን ሽፋን፣ ከሥራ እድል ፈጠራ አንጻር በተገኙ ውጤቶች ላይ ውይይት እንደሚደረግ አመላክተዋል፡፡

ሰኔ 22 ቀን 2016 ዓ.ም ሀገር አቀፍ የ2016/17 የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ይፋዊ ማስጀመሪያ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተገኙበት እንደሚከናወን ጠቁመዋል፡፡

በነሐሴ ወር 150 ሚሊዮን ችግኞችን በአንድ ጀንበር የመትከል መርሀ ግብር ይከናወናል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በዚህ መርሀ ግብርም በሚሸፈነው የመሬት ስፋት፣ በሚተከሉት ችግኞችና በተከላ በሚሳተፉት የሰዎች ብዛት በዓለም የድንቃድንቅ መዝገብ ለማስመዝገብ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ህንድ በአንድ ጀንበር 50 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል የያዘችውን ክብረወሰን ኢትዮጵያ በሦስት እጥፍ አሳድጋ 150 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል እየሠራች በመሆኑ በዚህ መርሀ ግብር ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ ተከላውን በማከናወን ዓላማውን ማሳካት ይገባል ሲሉ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለኢትዮጵያ የብልጽግና ጉዞ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሚና ከፍተኛ ነው!

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዋነኛ ዓላማ በሀገሪቷ ብቁ፣ ተነሳሽነትና የፈጠራ ክህሎት ያለው የሰው ኃይል በመፍጠር ዕድገትና ብልጽግናን ማረጋገጥ ነው። ሥራ ፈላጊ ሳይሆን ፈጣሪ ዜጋም ማፍራትም ነው። ዘርፉ ጊዜው የሚፈልገውን የሰለጠነ ሰው ኃይል ለገበያ በማቅረብና ፈጠራም በማበረታታት የማይተካ ሚና ይጫወታል።

ቴክኒክና ሙያ ዜጎች በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ተቀጥረውም ሆነ በራሳቸው ሥራ ፈጥረው ራሳቸውን፣ ቤተሰባቸውንና አካባቢያቸውን መቀየር የሚችሉበትን ሙያ የሚያስታጥቅ ከመሆኑም ባሻገር ኢንዱስትሪዎች ባልተቋረጠ መልኩ ክህሎት ያለው የሰው ኃይል እንዲያገኙም የሚያስችል ነው። የስልጠና ዘርፉ የሚያፈራው የሰው ኃይል ከኢንዱስትሪው ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለውና የሀገርንም የኢኮኖሚ አቅጣጫ የመወሰን አቅምም ያለው ነው።

ሆኖም በኢትዮጵያ በነበረው ሁኔታ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፉ በቂ ትኩረት የተሰጠው አልነበረም። የትምህርት ሥርዓቱ በበቂ ሁኔታ ዘርፉን ለመደገፍ ተነሳሽነት ያልነበረው ከመሆኑም ባሻገር ከዘርፉ ተመርቀው የሚወጡትም ተገቢው ዕውቅናና ክብር የሚሰጣቸው አልነበሩም። በዚህም ምክንያት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ለሀገር ማበርከት የሚገባውን አስተዋጽኦ ማበርከት ተስኖት ቆይቷል።

ይህንኑ ችግር በመረዳት በተለይ ከ1994 ወዲህ አዲስ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ከተገባ በኋላ መጠነኛ ለውጦች ቢመዘገቡም ካለው ዕምቅ አቅም አንጻር የተሄደበት ርቀት ግን ብዙም የሚያወላዳ አልበረም፡፡ በተለይም ተቋማቱ ሲቋቋሙ በቂ ጥናት ተደርጎባቸው አለመቋቋማቸው፤ የአካባቢያቸውን ጸጋ መሠረት አድርገው ወደ ሥራ አለመግባታቸውና ከኢንዱስትሪዎች ጋር ያላቸው ትስስርም የላላ መሆኑ ዘርፉ በሚፈለገው መልኩ እንዳይራመድ ማነቆ ሆኖ ቆይቷል።

ይህንኑ በመረዳት ከለውጡ ወዲህ መንግሥት የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴርን በማቋቋምና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕከላትን በማስፋፋት ለኢኮኖሚው ዕድገት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ በማድረግ ላይ ይገኛል። ሙያ ተቋማት ሲከፈቱ የአካባቢያቸውን ጸጋና ገበያ ማዕከል አድርገው እንዲከፈቱ በማድረግ፤ የተሻሻሉ ስልጠናዎች እንዲሰጡ በማድረግ እና ከኢንዱስትሪዎች ጋር ያለውን ትስስር በማጠናከር ዘርፉ በሀገር ልማት ውስጥ ተፈላጊ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል።

ከዚሁ ጎን ለጎንም የተቋማቱን አቅም በማጠናከር ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ጭምር በቴክኒክና ሙያ ተቋማት እንዲተኩ የማበረታታትና የመደገፍ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው። ዘርፉ ባገኘው ድጋፍም ቴክኒክና ሙያ ኢንዱስትሪዎቻችን ምርታማነታቸው እንዲያድግ እና ተወዳዳሪነታቸው እንዲጨምር በአመለካከቱም ሆነ በክህሎት የበቃ የሰው ኃይል የማቅረብ ሚናውን ለማሳደግ ተችሏል።

በተሠሩት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችም ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ይሰጠው የነበረው የተዛባ አመለካከት መሻሻል አሳይቷል። ዩኒቨርሲቲ መግባት የሚያስችል ውጤት ያላቸው ዜጎች በፍላጎታቸው ወደ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት መግባትም ጀምረዋል። በአጭር ጊዜ የሙያ ባለቤት፣ የሥራ ባለቤት እሆናለሁ የሚለውን አመለካከት መፍጠር ተችሏል።

በአጠቃላይ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፉ ኢትዮጵያ ለጀመረችው የዕድገትና የብልጽግና ጉዞ አጋዥ መሆን ጀምሯል። በተለይም የመንግሥት ዋነኛ ትኩረት የሆነውን ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በመተካትና ፈጠራን በማበረታታት ረገድ ዘርፉ እየተጫወተ ያለው ሚና ተስፋ ሰጪ ነው።

በአሁኑ ወቅት በርካታ ወጣቶች ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሰልጥነው በመውጣት አዳዲስ ፈጠራዎችን በማስተዋወቅ ላይ ይገኛሉ። በተለይም ለዲጂታል ዘርፉ የተሰጠውን ተኩረት በመጠቀም በርካታ ወጣቶች በጀማሪ ሥራ ፈጣሪነት (ስታርትአፕ) በመሳተፍ ከራሳቸው አልፈው ለበርካታ ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል።

ከባለ ሦስት እግሯ ባጃጅ እስከ ተንቀሳቃሽ አውቶሞቢል ፣ ከተንቀሳቃሽ ስልክ እስከ የግብርና ርጭት ማከናወኛ ድሮኖች፤ ኑሮን ከሚያቀሉ የቤት እቃዎች እስከ ግዙፍ ማሽነሪዎች፣ ለሕመም ፈውስ ወሳኝ የሆኑ የሕክምና መገልገያዎች እና ሌሎችም በርካታና ልዩ ልዩ ማሽነሪዎች ድረስ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕከላት በሚወጡ ወጣቶች እየተሠሩ የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ የበኩላቸውን ሚና በመወጣት ላይ ይገኛሉ።

ይህ ጅምር ተስፋ ሰጪ ውጤት የሚፈለገውን ግብ እስኪያሳካ በግንዛቤ ፈጠራ፣ በአመለካከት ለውጥ በተግባር የሚደረጉ ትኩረቶችና ድጋፎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል!


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ‹‹ኢትዮጵያ እንደምን ሠለጠነች?›› እንዲባል

ሚሊዮን ሺበሺ

ባለፈው ወር ‹‹ኢትዮጵያ እንደምን ሠለጠነች?›› በሚል ርዕስ የመሠልጠን ሂደቶችን ጅማሮ ማጠናከር እንዳለብን አይተናል። ዛሬ ደግሞ እስኪ የሰለጠኑ ሀገራትን ተሞክሮ እንመልከት። ወዲህ ደግሞ ባለፉት ሳምንታት ሲንጋፖር እንዴት እንደሠለጠነች የመንግሥት ከፍተኛ አመራሮች በዓይናቸው ያስተዋሉትን፣ በጆሯቸው የሰሙትን የሲንጋፖርን ተሞክሮ ሲናገሩ ነበር።

ፈጣን ሥልጣኔ፣ ፈጣን ዕድገት፣ ያልተጠበቀ ለውጥ፣ ከከፍተኛ ድህነትና ኋላቀርነት ወደ የዓለም ተፅዕኖ ፈጣሪነት በመለወጥ በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱ ሀገራት አንዷ ጃፓን ናት። ለመሆኑ ጃፓን እንደምን ሠለጠነች?

ደራሲ ከበደ ሚካኤል ከ20 ዓመታት በፊት የጻፏት ‹‹ጃፓን እንደምን ሠለጠነች?›› የምትል 120 ገጽ አነስተኛ መጽሐፍ አለች። ከበደ ሚካኤል ያቺን መጽሐፍ የጻፏት ኢትዮጵያም መለወጥ እንዳለባት ተሞክሮ ለማሳየት ነበር፤ ችግሩ ግን በተቆርቋሪነት ወደ ለውጥ መንገድ አልተሄደም ነበር። ለማንኛውም ከመጽሐፉ እና ከሌሎች ሰነዶች ባገኘነው መረጃ የጃፓንን የቀድሞ ታሪክ በጥቂቱ እናስታውስ፡፡

ጃፓን በጣም ድሃ እና እጅግ ኋላቀር የሆነ ልማድ የነበራት ሀገር ነበረች። ለውጥ ለማምጣት ያደረገቻቸው ጥረቶች በኢትዮጵያ ታሪክ ሆነዋል ሲባል ያልተሰሙ ናቸው። አንዱን ብቻ ልጥቀስ። ግራ ግብት ቢላት፤ መላ መስሏት፣ የሕዝብን ቁጥር በመቀነስ ችግሩ የሚቀረፍ መስሏት ማንኛውም ሰው ከሁለት ልጆች በላይ እንዳይወልድ ገደብ አደረገች። ይህን ክልከላ ተላልፋ ሦስተኛ ልጅ የወለደች እናት አንዱን መርጣ እንዲገደል ትሰጣለች። አስቡት! አንዲት እናት ከሦስት ልጆቿ ‹‹ይሄኛው ይገደል›› ብላ ስትሰጥ! ይህ በኢትዮጵያ ታሪክ በየትኛውም ዘመን ያልተደረገ ነው፤ ማድረግ ቀርቶ ያልታሰበ ነው። ዛሬ የዓለም ልዕለ ኃያል የሚባሉት እንደ ጃፓን ያሉ ሀገራት ግን እንዲህ አይነት ኋላቀርና ዘግናኝ ልማድ የነበራቸው ናቸው።

ታዲያ የሥልጣኔ አስጀማሪ፣ የሃይማኖትና የሞራል ባለቤት የነበረችው ኢትዮጵያ ለምን ይህን ያህል ጊዜ ድሃ ሆነች? ለምን ለዓይን ማራኪ የሆኑ ነገሮች የሏትም? ብለን ከጠየቅን ቆራጥ መሪ አልነበሯትም ማለት ነው። እነ ጃፓን አሁን የደረሱበት ላይ የደረሱት በአንድ ቆራጥ ንጉሥ እንደሆነ ታሪካቸው ያሳያል። ይህ ሰው ሙትሱሂቶ (ሜይጂ) ይባላል። ሙትሱሂቶ በጃፓን መሠልጠን ውስጥ፣ በጃፓን ማደግ ውስጥ፣ ለጃፓን እዚህ መድረስ፣ በአጠቃላይ ለዛሬዋ ጃፓን መነሻ ነጥብ ነው ብለው ያምናሉ።

በነገራችን ላይ የሙትሱሂቶን ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ስናመጣው ሙትሱሂቶ ሥልጣን የያዘው በ1860 ዓ.ም ልክ የኢትዮጵያው ንጉሥ አጼ ቴዎድሮስ የሞቱበት ዓመት ማለት ነው። አጼ ቴዎድሮስ ከጃፓኑ ንጉሥ በፊት የአውሮፓን ሥልጣኔ ለማምጣት ጥረት ያደርጉ እንደነበር የታሪክ ጸሐፊዎች ጽፈዋል፤ ተናግረዋል። ኢትዮጵያን የኢንዱስትሪ መንደር ለማድረግ አውሮፓውያንን ለመጠቀም ጥረት ያደርጉ ነበር። የእንግሊዝ ባለሙያዎችን ‹‹ሥሩልን›› እያሉ ይጠይቁ ነበር። ሴባስቶፖልን ያስጀመሩትም ለዚሁ ነበር።

አጼ ቴዎድሮስ ልክ እንደ ጃፓን ሃይማኖት ላይ ገደብ ጥለው ነበር። በቤተክርስቲያን ስም ብዙ ቦታ መባከን የለበትም፤ በቄስ ስም ይህ ሁሉ የሰው ኃይል ሥራ መፍታት የለበትም የሚል ዘመቻ ነበራቸው። አጼ ቴዎድሮስ ይህን ማድረጋቸው ‹‹ትክክል ነው! ትክክል አይደለም!›› አይደለም ጉዳዩ! ግን በሀገራቸው ለውጥ ለማምጣት ጥረት አድርገው ነበር ። የአውሮፓን ሥልጣኔ ለመኮረጅ ሀገራቸውን ልክ እንደ አውሮፓ ለማድረግ ጥረት አድርገው ነበር ነው። በዘመኑ ይጠቅማል ያሉትን ጥረት አድርገው ነበር፤ ችግሩ ግን የአጼ ቴዎድሮስ ታሪክ ጎልቶ የሚነገረው ሽጉጥ መጠጣታቸው ነው። የጀግንነት ምሳሌ የሚደረገውም ይሄው ሆነ።

ይህ የአጼ ቴዎድሮስ ጅምር አልቀጠለም። የኢትዮጵያ የውስጥም የውጭም ጣጣ እየባሰበት ሄደ። ለሥልጣን ሽኩቻ የሚደረጉ ጦርነቶች ሀገሪቱን ወደኋላ እየጎተቷት ሄዱ። እነሆ ይህ ችግር ዛሬ ድረስ ቀጥሎ ወደ ሥልጣኔ የሚወስድ ቆራጥ ውሳኔ ላይ አልደረስንም።

**አጼ ቴዎድሮስ ልክ እንደ ጃፓን ሃይማኖት ላይ ገደብ ጥለው ነበር። በቤተክርስቲያን ስም ብዙ ቦታ መባከን የለበትም፤ በቄስ ስም ይህ ሁሉ የሰው ኃይል ሥራ መፍታት የለበትም የሚል ዘመቻ ነበራቸው**

አሁን ኢትዮጵያ የሲንጋፖርን ተሞክሮ ለመውሰድ እየሠራች ነው። አዲስ አበባም በከፍተኛ መታደስ ላይ ናት። አራት ኪሎና ፒያሳን ያየ ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን ይረሳል። አዲስ አበባ ለዚያውም አራት ኪሎ ተወልዶ አድጎ፤ በሥራ አጋጣሚ ከ6 ወር በፊት ከአዲስ አበባ ውጪ የነበረ ሰው ዛሬ ድንገት አራት ኪሎ ቢጥሉት ሊጠፋ ሁሉ ይችላል። የሆነ አውሮፓ ሀገር ውስጥ ያለ ሊመስለው ይችላል። ይህ የሆነው በ6 ወር ውስጥ ነው። አሁን የተጀማመሩት ሲያልቁ ደግሞ በጣም ዘገየ ከተባለ ከ6 ወር በኋላ ብዙ ለውጦች ይታያሉ። በአጠቃላይ አዲስ አበባ በአንድ ዓመት ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ ታሳያለች ማለት ነው። ለአንድ ዓመት ያህል ከኢትዮጵያ ውጪ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ከአዲስ አበባ ውጪ ቆይቶ የሚመጣ ሰው ‹‹ አዲስ አበባ ይቺ ናት እንዴ?›› ሊል ይችላል። አፍንጫውን ይዞ ያልፍባቸው የነበሩት እነ ራስ መኮንን ድልድይ ቆሞ እንዲፈዝ ያደርጉታል።

ይህ የሥልጣኔ ጅማሮ ‹‹እንዴትና በማን መጣ?›› ነው ጥያቄው።

ኢትዮጵያ አሁን እየሠራችው ያለውን ነገር ለማስፈጸም ብዙ ቆራጥ ውሳኔዎች ተደርገው ነው። ብዙ ልማዳዊ ነገሮችን እና መሰናክሎችን በመቋቋም ነው። ለሺህ ዘመናት ሥር ሰደው የኖሩ አሳሪ ልማዶችን በመጋፈጥ ነው። እነ ጃፓን ከ150 ዓመታት በፊት ከነበሩበት እየተነሳች ነው ማለት ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ይህን ቆራጥ ውሳኔ ሲወስዱ የጃፓኑ ሙትሱሂቶ ወይም የኢትዮጵያው አጼ ቴዎድሮስ ያጋጠማቸውን ማህበረሰባዊና ልማዳዊ ጣጣ ተቋቁመው ነው። በ21ኛው ክፍለ ዘመን የሆነው የ19ኛውን ክፍለ ዘመን ልማድ እየተጋፈጡ ነው። የሀገርን ጉዳይ እና የፓርቲን ጉዳይ መለየት የማይችለውን የፖለቲካ ልማዳችንን ተቋቁመው ነው።

ስለዚህ ይህ ትውልድ ‹‹ኢትዮጵያ እንደምን ሠለጠነች?›› የሚለው ትርክት አካል ለመሆን ቆራጥ መሆን አለበት። ፖለቲካ እና ልማትን መለየት አለብን። ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ መንግሥትን መቃወም መብት ነው፤ መብት ስለሆነ ብቻም ሳይሆን መንግሥት ፖለቲካዊ ስህተት ሲሠራ መናገር ሥልጣኔ ነው። ዳሩ ግን ለሠሪው ባለሥልጣን ሳይሆን ለሀገር የሚሆኑ ነገሮችን መቃወም የጤና አይደለም፤ የሀገር ፍቅር መገለጫም አይደለም። ንጉሥ ላሊበላ ዛሬ በሕይወት የለም። ዳሩ ግን የላሊበላ ፍልፍል ዛሬ የኢትዮጵያ ሀብት ነው። እነሆ ከ900 ዓመት በኋላ ያለው ትውልድ እየኮራበት ነው። አክሱምን የሠራው ትውልድ ዛሬ የለም፤ ዳሩ ግን እነሆ የሥልጣኔ ምልክት አስቀምጦ ኢትዮጵያን በዓለም እንድትታወቅ አድርጓል።

ስለዚህ ከዓመታት በኋላ ‹‹ኢትዮጵያ እንደምን ሠለጠነች?›› እንዲባል ዛሬ እንሥራ!

# ነፃ ሃሳብ

# ሙያ ተኮር የክህሎት ማበልጸጊያ ተቋማት- ለሀገር እድገት

**ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽክታብ)**

አንድ ሀገር እውቀትን ከሙያና ከሥነ-ምግባር ጋር አቻችላ ወደፊት ለመጓዝ ሙያ ተኮር የክህሎት ማበልጸጊያ ተቋማት በብዛትና በጥራት እንደሚያስፈልጓት እሙን ነው። የነዚህ ተቋማት ሚና የእውቀት ትስስርና ሽግግርን በመፍጠር ቴክኖሎጂንና ፈጠራን በማበረታታት ለውጥና እድገት ከማምጣት አንጻር የማይተካ ሚና ይኖራቸዋል። ሀገራችን ኢትዮጵያም የሙያ ተቋማትን መሠረት ባደረገ መልኩ ለጀመረችው የለውጥና የተሐድሶ እንቅስቃሴ እንዲህ ያሉ ተቋማት እጅግ አስፈላጊ ናቸው።

ሙያ ተኮር የክህሎት ማበልጸጊያ ተቋማት ትውልድን በመቅረጽ ረገድ ላቅ ያለ ሚና ያላቸው ሲሆን በተለይም እውቀትን ወደተግባር በመለወጥ እና ችግር ፈቺ የሆኑ ፈጠራዎችን በማመንጨት በኩል የማይተካ ጠቀሜታ አላቸው።

ሀሳብ ወደተግባር ካልተለወጠ ብቻውን ትርጉም ላይኖረው ይችላል። አንድ ሀገር የቱንም ያህል የተማረ ዜጋ ቢኖራት እንደቴክኒክና ሙያ ያሉ የክህሎት ማበልጸጊያ ተቋማት በአይነትና በጥራት ከሌሏት የእውቀት መኖር ብቻውን ትርጉም አይሰጥም።

የእውቀት ሽግግር ተቋማት በእውቀት ዳብረው፣ በሙያ በልጽገው፣ አዕምሮን በማንቃት ትውልዱን ከጠባቂነት ወደሥራ ፈጣሪነት፣ ከተቀጣሪነት ወደቀጣሪነት፣ ከተቀባይነት ወደሰጪነት የሚያሻግሩ የዕድልና ድል መፍለቂያዎች ናቸው። እነኚህ የዕድልና ድል ማዕከላት ከግለሰብ እስከ ሀገር በሚደርስ ከዛም አልፎ ዓለም አቀፋዊነትን በከለለ መልኩ ስኬትን የሚያቀዳጁ የተሐድሶ ማዕከላት ናቸው።

የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ ብንመለከት መነሻቸው ቴክኒክና ሙያ እንደሆነ እንረዳለን። ኃያላን ሀገራት በቴክኖሎጂና በዘመናዊነት ነቅተውና በቅተው ጎልተውም የሚታዩት እውቀትን ወደተግባር በቀየረ የእውቀት ሽግግር ነው። ሙያ ተኮር የክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከል በእውቀት መር በሆነ እሳቤ ቴክኖሎጂ የሚባለውን የሥልጣኔ መሠረት ተንተርሶ እየተንቀሳቀሰ ያለ ዓለም አቀፍ ጽንሰ ሀሳብ ነው። በእንዲህ ያለው እሳቤ ታቅፈንና ዳብረን በፈጠራና በሙያ በክህሎትም አዲስ አስተሳሰብን ካልቀደድን በመጣንበት ነባር አቅጣጫ ተጉዘን ፍሬ ማፍራት የማይታሰብ ነው።

በፈጠራና ቴክኖሎጂው ዘርፍ እንደሀገር ከሚነሱብን ችግሮች መሐል አንዱ እውቀትን ወደመሬት የሚያወርድ የክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከል አለመኖሩ ነው። ቢኖር እንኳን ትውልዱ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋም አስተሳሰብ ተላቆ ፊቱን ወደቴክኒክና ሙያ እንዲሁም ወደ ተግባረ-ዕድ አለማዞሩ ነው። እነኚህ ማኅበራዊ ልምምዶች የተሐድሶ አቅጣጫን ሳይሰጡን በአድሮ ቃሪያ ፈሊጥ ለአንድ አይነት ክዋኔ ዳርገውን ሰንብተዋል። ለለውጥና ለእድገት በምናደርገው ጉዞ ላይ እውቀትና ሙያ በአንድ ቦታ ለፈጠራ የሚውሉበት የልህቀት ማዕከላት ያስፈልጉናል።

የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ከዩኒቨርስቲና ከከፍተኛ የትምህርት ማዕከላት በተሻለ መልኩ የልህቀት ማዕከላት ናቸው። እውቀትን ከሥነ-ምግባርና ከተፅዕኖ ፈጣሪነት ጋር አጋምደው ወደማኅበረሰብ የሚያንጸባርቁ የብርሃን ቀንዲሎች ናቸው። የብዙዎቻችን እውቀት ወደሀገርና ሕዝብ ሳይንጸባረቅ በጊዜ ሂደት የአገልግሎት ዘመኑ ያበቃ ነው። ልክ የጋን ውስጥ መብራት እንደሚባለው ርቀን ሳናበራ በእውቀትና በሙያችን ሌሎችን ሳናገለግል አንድ ቦታ በርተን የከሰምን ነን። እንዲህ አይነቱ ቆሞ ቀርነት ሙያን ከክህሎትና ከተራማጅ አስተሳሰብ ጋር ያለማቆራኘት፣ በሙያ ማበልጸጊያ ማዕከላት ሠልጥኖ ያለመውጣት መንስዔ የፈጠረው ነው።

ተምረን ወደመሬት ወርደን ሳንሠራና በክህሎት ዳብረን አዲስ ነገር ለሕዝባችን ሳንሰጥ ምንም ያህል ብንማር ዋጋ አናወጣም። እውቀት ዋጋ ያለው የሚሆነው በተግባር ሲገለጥ፣ ሀገርና ሕዝብን ስናገለግልበት ነው። እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ትውልዱ ራሱን ከዩኒቨርሲቲ ጋር አስተሳስሮ የሙያ ማዕከላትን ችላ ያለበት ሁኔታ ነበር። ስንማር ዩኒቨርሲቲን እያሰብን፣ ተመርቀን ከወጣን በኋላም ሥራን ፈጥሮ ከመሥራት ይልቅ መንግሥት ሥራ እንዲያስቀጥረን የምንጠብቅ ነን። በዚህ ሥነልቦና ውስጥ በቴክኖሎጂና በችግር ፈቺ ፈጠራ ራሷን የቻለች ሀገር መፍጠር አልቻልንም።

በአሁኑ ሰዓት መንግሥት በጀመረው የቴክኒክና ሙያ የክህሎት ማበልጸጊያ ንቅናቄ አዲስ አሠራርን እየተለማመድን እንገኛለን። ይሄ ልምምድ ትውልዱን ከክህሎትና ከሥራ ፈጣሪነት ጋር የሚያስተዋውቅ ወደ ዩኒቨርስቲ ብቻ ይመለከት የነበረውን ማኅበረሰብ ወደሙያ ማዕከላት እንዲያይና ሠልጥኖ እንዲወጣ፣ የጋን ስር መብራት የሆነውን ብዙኃን እውቀት ሰፊና ግዙፍ በማድረግ ወደሌሎች እንዲንጸባረቅ የሚረዳ እንቅስቃሴ ነው።

እንቅስቃሴው በመርሕና በመሪ ቃል ታጅቦ፣ በውይይትና በከፍተኛ አትኩሮት እየተመራ ያለ ነው። በጀት ተመድቦለት፣ ፖሊሲዎች ረቀውለት፣ ለክህሎት ምቹ በሆነ አካባቢ፣ በተሟላ የሙያ ማሠልጠኛ ማዕከል አሳቢ የሆነ አዲስ ትውልድ ለመፍጠር ብርቱ ትጋት እየተደረገ ይገኛል። የመጣንበትን የመማር ማስተማር አቅጣጫ የሚቀይር፣ ዲግሪ ከመያዝ በላይ እውቀትን ለሕዝብ እንዲጠቅም በክህሎት የማረቅ እንቅስቃሴ ከተልዕኮው አንዱን ነው።

ለአንድ ሀገር የለውጥ ዋስትና ከሆኑ የትውልድ ንቃት ውስጥ የመጀመሪያው እውቀትን ወደተግባር መቀየር ነው። በእኛ ሀገር እንዲህ አይነቱ ነገር እምብዛም አልነበረም። ለምን ካልን ታሪኮቻችን ከዩኒቨርስቲ ጋር ብቻ የተቆራኙ ስለነበር ነው። የለውጥ ዋስትና የሆኑ የትውልድ ንቃት በክህሎትና በቴክኒክና ሙያ ተቋም በኩል የሚገለጡ ናቸው። አዕምሮ የተረዳውን በተግባር የሚተረጉምበት፣ ለፈጠራና ለአዲስ እይታ የምንተጋበት የልህቀት ስፍራ ነው።

የክህሎት ማበልጸጊያ ተቋማት በትውልዱ ላይ የተለያዩ መገለጫዎች አሏቸው። ከነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ከፈላጊነት ወደሰጪነት፣ ከጠባቂነት ወደሥራ ፈጣሪነት፣ ከተገልጋይነት ወደአገልጋይነት የሚደረግ የለውጥና የተሐድሶ ጉዞ ነው። እነኚህ ገጸበረከቶች ከግለሰብ ወደቤተሰብ፣ ከቤተሰብ ወደማኅበረሰብ ላቅ ሲልም በዓለም አቀፍ ደረጃ የምንጠራበትን ዕድል የሚፈጥሩልን አጋጣሚዎቻችን ናቸው። እጆቻችን ለሥራ፣ አዕምሯችን ለለውጥ ካልተጋ ጥያቄ ምልክት ውስጥ ነን። እውቀት ኃይል ነው ስንል ችግር ፈቺና አገልጋይ ሲሆን ነው።

እንደሚታወቀው ሀገራችን በሁሉም ዘርፍ ለማለት በሚያስደፍር መልኩ በጠባቂነት ውስጥ ናት። ይሄ ትውልድ በእውቀት ዳብሮና በክህሎት በልፅጎ ከጠባቂነት ካላወጣት ሊታደጋት የሚችል ሌላ ኃይል የለም። ሁላችንም ኃላፊነት አለብን። መንግሥት ሁኔታዎችን በማስተካከልና ምቹ ከባቢን በመፍጠር እንዲሁም የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ለሀገርና ሕዝብ ዋጋ ያላቸው እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል። ቀሪው ማኅበረሰብ ለሙያ ተቋማት በጎ አመለካከትን በመፍጠር፣ ትውልዱ ለክህሎትና ለእጅ ሙያዎች ልዩ ፍቅር በመስጠት አዲስ ለውጥን ማምጣት ይቻላል።

ማር በማይሰጥ ቀፎ ብዙ ዓመታትን ደክመናል። ቀፎን መቀየር ሳይሆን አበቦች ወዳሉበት ሥፍራ መስቀል ለውጥ ያመጣል። ይሄ ማለት ትውልዱ አበባ በሌለበት ስፍራ ነበር እየዳከረ ያለው ማለት ነው። ለዛም ነው ድህነትን ማሸነፍ አቅቶን በተረጂነትና በጠባቂነት ስንማቅቅ የቆየነው። የክህሎት ተቋማት ደግሞ ራሳችንን የምንለውጥበት፣ ሕዝባችንን የምናገለግልበትን እድል የሚፈጥሩልን የብስለትና የብልህነት ማዕከላት ናቸው።

አሁን ስለምናወራው ጉዳይ የሚያትት በመረጃ ላይ የተደገፈ በፈረንጆቹ 2022 ላይ የወጣ አንድ ጥናት አንብቤ ነበር። የጥናቱ መነሻ ሀሳብ ኢትዮጵያውያን ለምን ድሀ ሆኑ? የሚል አንድምታ ያለው በጥያቄ የሚጀምር ሀሳብ ነው። እዛ ጥናት ላይ ለድህነታችን ዐበይት ምክንያት ሆነው ከተነሱት ውስጥ በቀዳሚነት የተጠቀሰው የሥራ ፈጠራ ክህሎት ውስንነት ነው። ሌሎቹን እንተዋቸውና በዚህ ጉዳይ ላይ ብንነጋገር እንኳን ብዙ ሀሳቦችን መለዋወጥ እንችላለን። ጥናቱ እንደምክንያት ያነሳው የክህሎት መበልጸጊያ ተቋማት አለመኖራቸው፤ ቢኖሩም በተገቢው መንገድ አለመጠቀማችን፣ እንደቴክኒክና ዕደ-ጥበብ ያሉ የሙያ ዘርፎች ቦታ ማጣታቸው፣ እውቀትን ወደተግባር አውርዶ አለመጠቀም የመሳሰሉትን ጠቅሷል።

> **የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ከዩኒቨርስቲና ከከፍተኛ የትምህርት ማዕከላት በተሻለ መልኩ የልህቀት ማዕከላት ናቸው። እውቀትን ከሥነ-ምግባርና ከተፅዕኖ ፈጣሪነት ጋር አጋምደው ወደማኅበረሰብ የሚያንጸባርቁ የብርሃን ቀንዲሎች ናቸው**

እንደአጋጣሚ ሆኖ የጥናቱ ውጤት አሁን እኛ እንደችግር ካነሳነው እውነታ ጋር የተመሳሰለ ሆኗል። መንግሥትም ቀድሞ በመንቃት እስከ ተወካዮች ምክር ቤት በደረሰ ርቀት በአሁኑ ሰዓት ልዩ አትኩሮት በመስጠት እንቅስቃሴ እያደረገበት ይገኛል። ለውጥ ከመንግሥት ወደሕዝብ፣ ከሕዝብ ወደመንግሥት ነው። የሙያ ማዕከላት ግን ከማንም ወደማንም አይደሉም። ዓለም ራሷን የቀየረችበት፣ ኃያላኑ ከድህነት የወጡበት ስለሆነ ያለማንም አስገዳጅነት ልንጠቀምበት የሚገባ ነገር ነው።

የጀርመንና የቻይና ሥልጣኔ መነሻውን ያደረገው ቴክኒክና ሙያን ነው። የነዚህ ሀገር የቴክኖሎጂና የኃያልነት ሚዛን በክህሎትና በሥራ ፈጣሪነት ላይ የተመሠረተ ነው። የዛሬ ስልሳ ዓመት ገደማ ቻይና ከወደቀችበት ስትነሳ እንደምርኩዝ የተደገፈችው የክህሎት መርሆችን ነው። ለዚህም ትውልዱ ሙያ ማዕከላት ውስጥ ገብቶ እውቀት እንዲቀስም፣ ሙያ እንዲለምድ፣ ከችግር ፈጣሪነት ወደችግር ፈቺነት እንዲሸጋገር ንቅናቄ ጀመረች። ያ ንቅናቄ ፍሬ አፍርቶ ቻይናን በዓለም ላይ ካሉ በሁሉም ነገር ከተሳካላቸው ሀገራት አንዷ እንድትሆን አደረጋት።

የጀርመንም የለውጥና የተሐድሶ ተሞክሮ ከዚህ የሚነሳ ነው። እንደነበረ የሚቀጥል ምንም ነገር የለም። የዓለም መልክ ወደሥራ ፈጣሪነት ተቀይሯል። እኛም ከስንፍና ወደትጋት፣ ከስልቹነት ወደታታሪነት በመቀየር እንደጀርመንና ቻይና ታሪካችንን ማደስ ይኖርብናል። ሀገራችን የምትታማበት አንዱና ዋነኛው ጉዳይ እውቀትን ወደተጨባጭ እውነታ የሚቀይር የሙያ ተቋማት አለመኖራቸው ቢኖሩም ንድፈ ሀሳብን ወደተጨባጭ እውነታ በመቀየርና የዕደ-ጥበብ ባለሙያዎችን ማብቃት አለመቻል እንደሆነ ለሁላችንም ግልጽ የሆነ እውነት ነው። ከፊተኞቻችን ተምረን ራሳችንን ለለውጥ ማዘጋጀት የዚህ ትውልድ ተግባር መሆን አለበት።

ሰባና ሰማኒያ ከመቶው ወጣት በሚኖርባት ሀገር ላይ ሩቅ በማይወስድ መንገድ ላይ መፍገምገም አጉል ነው። ወጣቱ እጆቹን አፍታቶ ተዐምር እንዲሠራና አዕምሮውን ተጠቅሞ ለሀገር የሚበጅ ቁም ነገር እንዲያደርግ የክህሎት ማበልጸጊያ ተቋማት በእጅጉ ያስፈልጉናል። ጊዜያችንን ከኃይላችን ጋር አጣጥመን በክህሎት በልጽገን ሩቅ ለመሄድ ሙያ የምንቀስምባቸው የአእምሮ መበልጸጊያ ስፍራዎች ሊኖሩን ግድ ይላል።

ትኩስ ኃይል አለን። ለለውጥና ለእድገት የተሰናዳን ነን። እኚህ ፍላጎቶቻችን ሁነኛ ቦታ ካላገኙ ባክነው ነው የሚቀሩት። የሕዝብ ቁጥር ብቻውን አንድን ሀገር ከድህነት አይታደጋትም። በክህሎት ካልተገራ የወጣት መብዛት ብቻውን ለውጥ አያመጣም። ለውጥና እድገት ያለው ለአእምሮ ምቹ ስፍራን በማዘጋጀትና እውቀትን ወደተግባር በሚቀይር ተቋም በኩል ነው። እንደሀገር የጀመርነው እንቅስቃሴ ፍሬ አፍርቶ በሙያና በክህሎት የበሰለ ትውልድ እንደሚፈጠር እናምናለን።

ሩቅ የማይወስዱ መንገዶች ትርፋቸው ድካም ነው። አቅጣጫችንን ቀይረን ትርፍ ባለውና እሴት በሚጨምር የሙያ ዘርፍ ላይ በመሰማራት ራሳችንንና ሀገራችንን ነፃ ማውጣት እንችላለን። የመማር ማስተማሩ የስምሪት አቅጣጫ ወደ ዩኒቨርስቲ ብቻ ነበር። የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶች ተማሪ አጥተው ተዘግቶባቸው ከርመዋል። አዋጪና ለዋጪ ባልሆነ የእውቀት ስም ተምረን ጥቅም ሳንሰጥ እንዲሁ የቀረን አለን።

አዲስ እይታ ያስፈልገናል። ጊዜን ከእውቀት ጋር፣ ሙያን ከክህሎት እና ከሥነምግባር እንዲሁም ከፈጣሪነት ጋር ያቆራኘ የመማር ማስተማር ሥርዓት የነበረውን በመሻር በትውልዱ ላይ ንቃትን የሚፈጥር ነው። ሀሳብ አመንጪነትን ከትጋትና ከታታሪነት ጋር አጣጥመው የሚሄዱ፣ ተምሮ ሥራ ለመፈለግ ሳይሆን ተምሮ ለማስተማር፣ ሠልጥኖ ለማሠልጠን፣ አውቆ ለማሳወቅና ሙያውን ለሌሎች ለማጋራት የበረታ የክህሎት ማዕከላት የዚህ ዘመን የትውልዱ ስጦታዎች እንዲሆኑ በመመኘት ላብቃ ቸር ሰንብቱ።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# የወጣቶች ተሳትፎና ተሰሚነት እንዲያድግ

ክብረዓብ በላቸው



የተለያዩ የማኅበራዊ ሳይንስ መረጃዎች ወጣት የሚለውን ፅንስ-ሃሳብ የእድሜ ክልልን መሠረት አድርገው ሲተነትኑ ይስተዋላል፡፡ አንዳንዶች ደግሞ እድሜንና የትምህርት ደረጃን መሠረት በማድረግ የወጣትነትን ክልል ይወስናሉ፡፡ በኢትዮጵያ በ1996 ዓ.ም የወጣው ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ ከ15 እስከ 29 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘውን የኅብረተሰብ ክፍል ወጣት ብሎ ይደነግጋል፡፡

ወጣቶች አፍላ የልማትና የዴሞክራሲ ኃይሎችና ሀገር ተረካቢ ዜጎች ናቸው፡፡ በትምህርት የታነፀና የተገነባ አቅም ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የማኅበራዊ ሳይንስ ምሁራን ወጣትነት ቅን አመለካከት የሚስተዋልበት፣ አካላዊና አዕምሯዊ ችሎታና ብቃት የሚዳብርበት፣ በጥንካሬ የታጀበ እና ለሥራ ምቹ፣ ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ አቅም ነው ይላሉ፡፡ እናም፣ ወጣቶች አፍላ ኃይል በመሆናቸው ፖሊሲዎችና በዕቅዶች ዝግጅት ተሳትፈው መወሰን ከቻሉ እና የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ በመንግሥትና በሚኖሩበት ማኅበረሰብ እውቅና ከተሰጠው ትልቅ ሚና ያላቸው ሰብዓዊ ሀብቶች ናቸው በማለት ወጣትነትን ይገልጻሉ፡፡

የኢትዮጵያ ወጣቶች በሀገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገት የማይተካ ድርሻ ያላቸው እንደመሆኑ በተለያዩ ዘርፎች የሚኖራቸው ተሳትፎ ማደግ እንዳለበት ብዙዎች ይናገራሉ።

በቅርቡ የሴቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መርጃ ድርጅት (ዩኒሴፍ) ጋር በመተባበር የታዳጊ ወጣቶች እና ወጣቶች ዲጂታል ተሳትፎ መድረክ የሆነውን ዩ-ሪፖርት የተሰኘ የአፕ መተግበሪያ ይፋ አድርጓል። መድረኩ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) በተገኙበት ነው በይፋ የተጀመረው። በተጨማሪም አቡባካር ካምፖ (ዶ/ር)፣ የዩኒሴፍ የኢትዮጵያ ተወካይ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ የለጋሽ ማኅበረሰብ አባላት፣ የሲቪል ማኅበራትና፣ ወጣቶች በመድረኩ ተገኝተዋል።

እኤአ በ2011 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በዑጋንዳ የጀመረውና በአሁኑ ወቅት ከ 90 በላይ ሀገራት እና በዓለም አቀፍ ደረጃ 35 ሚሊዮን ተጠቃሚዎችን ማፍራት የቻለው ይህ መተግበሪያ፣ ታዳጊዎች እና ወጣቶች በሚመለከቷቸው ጉዳዮች ላይ እንዲናገሩ እና ጠቃሚ የሕይወት አድን መረጃዎችን እንዲያገኙ የሚያስችል ነው ተብሏል። ላለፉት 13 ዓመታት ዩ-ሪፖርት ከተለያዩ አካላት ጋር በሠራው ሥራ ለውጥ ማምጣት መቻሉም ተገልጿል።

መተግበሪያውን ይፋ ያደረጉት የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ክብርት ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር)፥ መተግበሪያው የሀገራችን ወጣቶች በተለይ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲለዋወጡ እና ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኙ ያግዛል ብለዋል። በተጨማሪም ለፖሊሲ አውጪዎች ግብዓት የሚሆኑ ሃሳቦችን ከወጣቶቹ ለማሰባሰብ የሚያስችል ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት የጎላ ፋይዳ ይኖረዋል ብለዋል።

የወጣቶችን ድምፅና ሃሳብ የምንሰማበት ትክክለኛው ጊዜ አሁን ነው ያሉት ክብርት ሚኒስትሯ ወጣቶች መተግበሪያውን በመጠቀም ለዘላቂ ሠላምና ፀጥታ እንዲሁም ለጠንካራ ሀገረ መንግሥት ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ማበርከት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

በተለይ በአሁኑ ጊዜ ሀገራችን ኢትዮጵያ ዘላቂ ሠላም ለማስፈንና ሁለንተናዊ ብልፅግናን ለማረጋገጥ በጥልቀት እየመከረች የምትገኝ ወቅት በመሆኑ ወጣቱ በንቃት እንዲሳተፍ ጥሪ አቅርበዋል። ወጣቶች መተግበሪያውን ፍሬያማ በሆነ መንገድ፣ በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት እንዲገለገሉበትም በአፅንዖት አሳስበዋል።

ኤርጎጌ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፣ ኢትዮጵያ ይህንን መተግበሪያ ጥቅም ላይ እንዲውል ስታደርግ ሌሎች ሀገራት ያላቸውን ተሞክሮ በማየትና ምን ያህል መንግሥት የሚያወጣቸው ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ ይረዳል? የሚለውን ከሚመለከታቸው ሌሎች የመንግሥት ተቋማት ጋር ማለትም ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር እንዲሁም ከኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አስተዳደር (ኢመደአ) ጋር ተደጋጋሚ ውይይት በማድረግ ወደ ሥራ እንዲገባ ስለመደረጉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ካላት የሕዝብ ቁጥር 70 በመቶ የሚሆነው ወጣት እንደሆነ የተነገሩት ኤርጎጌ(ዶ/ር)፣ የዚህ ወጣት ድምፅ ተሰሚነት ሊኖረው እንደሚገባ ገልፀው፣ በተለይ ፖሊሲ አውጪ የሆኑ አካላት ወጣቱ የሚፈልገውን ነገር በመለየት ለተግባራዊነቱ መሥራት እንዳለባቸው አሳስበዋል።

ዶክተር ኤርጎጌ፣ ዩ-ሪፖርት ወጣቶች በራሳቸው በአካባቢያቸው የሚያዩትን ችግር ለመፍታትና እንደ ወጣት ከፍተኛ ችግር ሆነው ያሉ ጉዳዮችን ለሚመለከታቸው አካላት እንዲያቀርቡና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ይህንን መሠረት አድርገው የተለያዩ ሥራዎችን እንዲሠሩ በዚህም የወጣቱን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንዲችሉ አቅጣጫ እንደሚሰጥ ይናገራሉ።

የዩ ሪፖርት መተግበሪያ ወጣቱን በተመለከተ የተለያዩ ጥናቶችን ለመሥራት የሚወስደውን ረዥም ጊዜ በማስቀረት በአጭር ግዜ የወጣቱን የልብ ትርታ ማየትና ማወቅ የሚቻልበትን መንገድ እንደሆነ የሚናገሩት ሚኒስትሯ፣ መተግበሪያው ወጣቶች ድምፃቸውን ከማሰማት ባሻገር በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ተሳታፊ ሆነው ከመንግሥት ጋር በቅንጅት እንዲሠሩ የሚያስችል እንደሆነ ተናግረዋል።

በተለይ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ አካታች ሀገራዊ ምክክር ለማድረግ እንቅስቃሴ እያደረገች ባለችበት ሰዓት የወጣቱ ድምፅ የሚሰማ መሆኑን እርግጠኛ መሆን ይኖርብናል የሚሉት ክብርት ሚኒስትሯ፣ ቴክኖሎጂው ሀገራዊ ምክክሩን ጨምሮ በትምህርት፣ በጤና፣ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የወጣቶችን ተሰሚነት የሚያሳድግ ነው ይላሉ።

እስከአሁን ከአስራ ሦስት ሺህ በላይ በዚህ መተግበሪያ የተመዘገቡ ወጣቶች አሉ የሚሉት ኤርጎጌ (ዶ/ር)፣ ማኅበራዊ ሚዲያው ትክክለኛ ባልሆኑ መረጃዎች በተሞላበት በዚህ ወቅት ይህ ቴክኖሎጂ መኖሩ ትክክለኛ መረጃ በመለዋወጥ ማኅበረሰብን ለመለወጥ የሚሠሩ ሥራዎችን በመደገፍ የሚኖረው ፋይዳ ትልቅ እንደሆነ ይናገራሉ።

እንደ ሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ደግሞ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶችን ለማሳለጥ፣ የወጣቱን ስብዕና ለመገንባትና ከአልባሌ ሱሶች ተላቀው አምራች ዜጋ መሆን እንዲችሉ የተለያዩ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል የቴክኖሎጂ አማራጭ ይዞ የመጣ ነው ይላሉ።

በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢ የሚገኙ ወጣቶች ስለቴክኖሎጂው መረጃ አግኝተው መጠቀም እንዲችሉ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የኢትዮጵያ ወጣቶች ካውንስልን ጨምሮ ከተለያዩ አጋር አካላትና ሚዲያዎች ጋር ሰፊ ሥራዎችን የመሥራት እቅድ እንዳለው የሚናገሩት ዶክተር ኤርጎጌ፣ በዚህ ረገድ የሚዲያ ተቋማት ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጋር በጋራ ለመሥራት ዝግጁ እንዲሆኑ ጥሪ አቅርበዋል።

የኢንተርኔት አገልግሎት ማግኘት የሚችሉ ሁሉም ወጣቶች በዚህ መተግበሪያ አማካኝነት ሀሳባቸውን መስጠት እንደሚችሉ የሚናገሩት ኤርጎጌ (ዶ/ር)፣ ወደዚህ ቴክኖሎጂ የሚቀላቀሉ ወጣቶች በኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት የራሳቸውን ድርሻ ማበርከትና ድምፃቸውን ማሰማት እንዳለባቸው ተናግረዋል።

> **ወጣቶች አፍላ የልማትና የዴሞክራሲ ኃይሎችና ሀገር ተረካቢ ዜጎች ናቸው፡፡ በትምህርት የታነፀና የተገነባ አቅም ሊኖራቸው ይገባል**

ይህ መተግበሪያ በተለያዩ ሀገራት ጥቅም ላይ ውሎ የአመለካከትና የዕድሜ ልዩነት ውስጥ ያለውን ወጣት ማለትም ሴት ወጣቶች፣ አፍላ ወጣቶች፣ በሱስ ውስጥ ያሉ ወጣቶች፣ የጤና እክል የሚገጥማቸው ወጣቶች፣ የአካል ጉዳተኛ ወጣቶች፣ በገጠርና በከተማ ያለ ወጣት በአጠቃላይ በዘርፈ ብዙ የሕይወት ልምምድ ውስጥ ያሉ ወጣቶችን እንዴት መስተዳደር እንዳለባቸው ትምህርት የሰጠ ቴክኖሎጂ ነው ያሉት ኤርጎጌ (ዶ/ር)፣ ኢትዮጵያም ይህንን ልምድ በመቅሰም ሥራ ላይ እንዳዋለችው ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ የዩኒሴፍ ተወካይ አቡባካር ካምፖ (ዶ/ር) በመድረኩ እንደተናገሩት “ወጣቶች በማንኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ አዎንታዊ እድገት ለማምጣት ትልቅ አቅም እንዳላቸው ገልፀው “በትምህርት፣ በክህሎት ግንባታ እና ምቹ አካባቢን በመፍጠር ዩኒሴፍ ከመንግሥታት እና ከሌሎች አጋሮች ጋር በመሆን ወጣት ኢትዮጵያውያን ሙሉ አቅማቸውን ጥቅም ላይ እንዲያውሉና ለማኅበረሰባቸው ትርጉም ያለው አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ያደርጋል ብለዋል።

አቡበከር (ዶ/ር) ‘U-Report Ethiopia’ ለአጠቃቀም ምቹና ቀላል የአፕ መተግበሪያ ሲሆን በ99 የዓለም ሀገራት ተግባራዊ ሲደረግ የነበረ መሆኑንና ኢትዮጵያን 100ኛ ሀገር ሆና መቀላቀሷን ገልጸዋል። አብዛኛው ወጣት የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ ለማድረግና ለማብቃት ታስቦ መዘጋጀቱንና ወጣቶችም በንቃት እየተሳተፉበት ያለ ውጤታማ መተግበሪያ ለመሆኑ የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ በማሳያነት አቅርበዋል።

አብዛኛው ወጣት የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ ለማድረግና ለማብቃት ታስቦ መዘጋጀቱንና ወጣቶችም በንቃት እየተሳተፉበት ያለ ውጤታማ መተግበሪያ ለመሆኑ የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ በማሳያነት አቅርበዋል።

ተወካዩ በተጨማሪነት መድረኩ የጤና መረጃን ለማሰራጨት እና ግንዛቤን ለመፍጠር በተለይም በበሽታዎች ወቅት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል ያሉ ሲሆን ለምሳሌ በዛምቢያ በዩ-ሪፖርት ተፅዕኖ ምክንያት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የኤችአይቪ ምርመራ መጠን ከ24 በመቶ ወደ 40 በመቶ ጨምሯል። የወጣቶች ድምፆች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሰሙ ነው፣ ተቋማዊ ተግባራት ላይ በጎ ተፅዕኖ እያሳደሩ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያደረጉ እንደሆነ ተናግረዋል።

በመጨረሻም ክብርት ሚኒስትሯ ለመተግበሪያው እውን መሆን ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ዩኒሴፍ እና የኢትዮጵያ ወጣቶች ምክር ቤት ላደረጉት ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል።

ሌላው የመተግበሪያ ማስተዋወቂያ መድረክ አስተባባሪና የኮሚቴ አባል የሆነው ወጣት ጉዲሳ እንደሚናገረው፣ ኢትዮጵያ ሰፊና ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወጣት የሚኖርባት ሀገር እንደመሆኗ ቴክኖሎጂው በየአካባቢው ያለው ወጣት በተለያዩ ጉዳዮች ማወቅ ያለበትን ነገር እንዲያውቅና ፍላጐቱን፣ ስሜቱን፣ እንዲገልጽ የሚያስችል መተግበሪያ እንደሆነ ይናገራል።

ለአብነት ስለሀገራዊ ምክክሩ ወጣቱ ምን ያህል ግንዛቤ አለው በሚል ጥያቄ በመውጣት የወጣቶችን ሀሳብ ለማዳመጥ ሙከራ ተደርጎ እንደነበር የሚናገረው ጉዲሳ፣ ስለ ምክክር ሰምቷል ወይ? ምን ተሳትፎ እያደረገ ነው? ስለ ምክክሩ ጠቀሜታ ምን ያህል መረዳት አለው? የሚለውን ይህ መተግበሪያ በቁጥርና በዳታ በመለየት አስፈለጊ መረጃ መስጠት የሚችል ነው ይላል።

ይህንን መተግበሪያ በመጠቀም ከወጣቶች የሚመጡ ምላሾችን በመውሰድ ወጣቱ ምን ያሳስበዋል? ምን አይነት ትኩረት ይፈልጋል? የሚለውን የተለያየ ዳታ በመሰብሰብ ለውጥ እንዲመጣ እንሠራለን የሚለው ጉዲሳ፣ ይህ ሥራ ከተሠራ በኋላ ሪፖርት በማውጣት ለሚመለከታቸው የፖሊሲ አውጪዎች በማጋራት የወጣቱን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እንደሚውል ይናገራል።


በተለያዩ ክልሎች በመሄድ ስለ መተግበሪያውን ምንነትና ጠቀሜታ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ በቀጣይ እንደሚሠራ የተነገረው ጉዲሳ፣ በሂደት ቴክኖሎጂውን በመላው ሀገሪቱ በማላመድ ወጣቶችን በሚመለከት የትኛውም ፖሊሲ ከመውጣቱ በፊት የጉዳዩ ባለቤት የሆኑ ወጣቶች ሀሳብ እንዲሰጡ ማድረግ እንዲቻል ዕድል የሚሰጥ ነው ይላል።

ወጣቶች ዩ-ሪፖርትን በበርካታ ማኅበራዊ ሚዲያዎች፣ በቴሌግራም፣ በዋትስአፕ እና በፌስቡክ በኩል ማግኘት ይችላሉ የሚለው ጉዲሳ፣ በተለያዩ ጉዳዮች ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ምን ያህል ወጣቱ ስለ ጉዳዩ ግንዛቤ አለው የሚለውን በመለየት የመፍትሔ ሀሳብ ለማምጣት እንደሚረዳ ተናግሮ፣ ወጣቶች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ አቅርቧል።

# የምድር በረከት

## ኮርፖሬሽኑ ወርቅ በማምረት ሂደት እያሳየ ያለው ተስፋ ሰጪ ጅማሮ

**ወርቅነሽ ደምሰው**



**የኢትዮጵያ ማዕድን ኮርፖሬሽን በማዕድን ልማት ዘርፍ ተሠማርተው ከሚሠሩት ተቋማት መካከል ተጠቃሽ ነው። ኮርፖሬሽኑ የረጅም ጊዜ ልምድ ስላለው የተለያዩ ማዕድናትን እያመረተ ይገኛል**

ኢትዮጵያ ከፍተኛ መጠን ያለው የወርቅ ክምችት እንዳላት ይነገራል። በሀገሪቱ እስካሁን በተደረገ የዳሰሳ ጥናት ከ517 ቶን በላይ የወርቅ ክምችት መኖሩ ተረጋግጧል። ይሁን እንጂ ይህን ሀብት በማልማት ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረጉ ሂደት እምብዛም አልተሠራበትም። አሁን ላይ ግን መንግሥት ለማዕድን ዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ ሥራዎች እየተሠሩ በመሆናቸው መሻሻሎችና ለውጦች እየመጡ መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ።

በተለይ በማዕድን ልማት ላይ ተሠማርተው የሚሠሩ ኩባንያዎችና ተቋማት ሀብቱን ከማልማት አንጻር ሥራዎች እየሠሩ ይገኛል። የኢትዮጵያ ማዕድን ኮርፖሬሽን በማዕድን ልማት ዘርፍ ተሠማርተው ከሚሠሩት ተቋማት መካከል ተጠቃሽ ነው። ኮርፖሬሽኑ የረጅም ጊዜ ልምድ ስላለው የተለያዩ ማዕድናትን እያመረተ ይገኛል። በተለይ ሜታሊክ ሚኒራል ከሚባሉት ውስጥ ወርቅ በማምረት ረገድ በርካታ ሥራዎች በመሥራት ላይ ይገኛል።

አቶ ሳዲቅ ከቢር የኢትዮጵያ የማዕድን ኮርፖሬሽን ከፍተኛ የማዕድን ባለሙያና የሥነ ምድር ተመራማሪ (ጂኦሎጂስት) ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት፤ ኮርፖሬሽኑ በማዕድን ዘርፍ የታወቀና ትልቅ ሥራን ሲሠራ የቆየ ነው። ቀደም ባሉት ጊዜያት በሀገር ደረጃ በሜታሊክ ሚኒራል ማዕድናት ዘርፍ ትልቅ ልምድ ካላቸው ተቋማት አንዱ ነው። ባለፉት ዓመታት ከነበረው ለውጥ ጋር ተያይዞ ሲሠሩ የነበሩት ሥራዎች የተቀዛቀዙ ቢሆንም የተለያዩ አማራጮችን በመውሰድ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ።

ኮርፖሬሽኑ በተለይ በኢትዮጵያ የታወቀ የታንታለም ማዕድን ብቸኛ አምራች እንደነበር ጠቁመው፤ በኦሮሚያ ክልል ጎጂ ዞን የታንታለም ማዕድን ሲያመርት ቆይቶ በተለያዩ ምክንያቶች ማምረት ካቆመ ሰባት ዓመት በላይ መሆኑን አቶ ሳዲቅ ይናገራሉ።

ኮርፖሬሽኑ በተለይ የወርቅ ማዕድን ለማምረት የተለያዩ አማራጮችን ወስዶ በርካታ ሥራዎች እየተሠራ መሆኑን ያመላክታሉ። በጋምቤላ ክልል 100 እስኩዌር ኪሎ ሜትር ቦታ ላይ ጥናት ለማድረግ ፈቃድ ወስዶ ጥናት እያካሄደ ሲሆን፤ በዘንድሮ ዓመትም ሁለተኛ ዙር ጥናት የተካሄደ መሆኑን ይገልጻሉ።

እንደእሳቸው ማብራሪያ፤ ወርቅ ጽንሰ ወርቅ እና ደለል ወርቅ ተብሎ በሁለት ዓይነት መንገድ ይጠናል። ጽንሰ ወርቅ በጣም ወደታች ተገብቶ የሚወጣና ተፈጭቶ በትልቅ ቴክኖሎጂ የሚመረት ነው። ደለል ወርቅ ግን ከላይ ያለው ድንጋይ በተለያዩ ምክንያቶች ሲበሰብስና ሲፈረካከስ ከዚያ ውስጥ ሊወጣ የሚችል የወርቅ አይነት ነው። ወርቅ አብዛኛውን ጊዜ ከተራራ የሚገኝ ሲሆን፤ በውሃ ወይም በንፋስ ዝቅ ወዳለ ቦታ እየሄደ ይመጣና ይከማቻል ይህ ሲሆን ደግሞ በአነስተኛ ቴክኖሎጂና በትንሽ ወጪ ሊመረት ይችላል።

ኮርፖሬሽኑ ጋምቤላ ክልል ሁለቱንም አይነት ወርቅ ለማምረት እየሠራ መሆኑን አቶ ሳዲቅ አመላክተዋል። ከዚህ በተጨማሪም በኦሮሚያ ክልል ጉጂ ዞን ከአነስተኛ የወርቅ አምራች ማኅበራት ጋር አብሮ በመሥራት ቴክኖሎጂና ወጪውን በመሸፈን በሰፊው እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በቅርቡም ደለል ወርቅ ማምረት እንደሚጀምር ይገልጻሉ። በተመሳሳይ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል እንደዚህ አይነት ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አስታወቀዋል።

ኮርፖሬሽኑ በወርቅ ማዕድን በጋምቤላ፣ በኦሮሚያ ክልል እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ላይ ሰፋፊ ሥራዎች እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይ በጉጂ ዞን 500 በላይ ሠራተኞች፣ ሰፊ ቦታዎች እና ወርክሾፖች ስላሉት በስፋት እየሠራበት እንደሚገኝ ገልጸዋል። በመመሪያ ደረጃ ደለል ወርቅ የሚያመርት ቢሮም ስላለው ሥራው በሰፊው ስለሚሠራ ይህን ለማሳለጥ ያስችል ዘንድ ከኦሮሚያ ማዕድን ቢሮ ጋር ለመሥራት ስምምነት ላይ ተደርሷል ብለዋል።

በተመሳሳይ እንዲሁ ታንታለም በማምረት ረገድም አሁን ላይ በጉጂ ዞን ታንታለም የሚያመርቱ ብዙ አነስተኛ አምራች ማኅበራት ያሉ መሆኑን ጠቅሰው፤ ኮርፖሬሽኑ ከእነዚህ ማኅበራት የታንታለም ማዕድን በመግዛት ለውጭ ገበያ ለመላክ የሚያደርገውን ዝግጅት እያጠናቀቀ ይገኛል ብለዋል። በሌላ በኩል ኮርፖሬሽኑ የተሟላ የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂው ስላለው ቀደም ሲል ታንታለም ያመርትበት በነበረው ቦታ በድጋሚ እንዲሰጠው ጥያቄ አቅርቦ ምላሽ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል። ምላሽ እስኪያገኝ ድረስ ማዕድን በሕገወጥ መልኩ ከሀገር ከሚወጣና ከሚባክን በሚል ማዕድኑን በመግዛት ወደውጭ በመላክ ገቢን የማስገኘት ሥራ እየተሠራ መሆኑን ያስረዳሉ።

የሜታሊክ ሚኒራል ኮፐር፣ የብረት ማዕድን እና የመሳሰሉ ማዕድናትንም ይይዛል። ከዚህ ውስጥ አንዱ የሆነው የኮፐር ማዕድን በቤንሻንጉል ክልል አለ እየተባለ መሆኑን የገለጹት አቶ ሳዲቅ፤ ኮርፖሬሽኑ ወደ ክልሉ በመሄድ ለጥናት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

እንደሳቸው ማብራሪያ፤ በዘንድሮ በጀት ዓመት በማዕድን ዘርፉ በጋምቤላ ክልል ጽንሰ ወርቅና ደለል ወርቅ ለማግኘት ጥናቶች ተደርገዋል። የደለል ወርቅ የሚባል በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊመረት የሚችል የወርቅ አይነት ሲሆን፤ በጥናቱ መሠረት በሚቀጥለው ዓመት ሥራ የሚጀመርበት የተባለ ሦስት እስኩየር ኪሎሜትር ቦታ ተለይቷል። ከዚህም 200 ኪሎግራም ወርቅ ይገኛል ተብሎ ተገምታል። ይህንንም ለማዕድን ሚኒስቴር በማሳወቅ የማምረት ፈቃድ ለማግኘት ጥያቄ በማቅረብ እንደተፈቀደልን ወደ ሥራ የሚገባ መሆኑን አመላክተዋል።

"አሁን ላይ ያለው የወርቅ አመራረት ሂደትም ሆነ ከተመረተ በኋላ ያለ ሕገወጥነት መንግሥት ከዘርፉ ሊያገኝ የሚገባው ጥቅም እንዳያገኝ እያደረገ ነው። በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ ሥራውን ቢጀምር ይህ ችግር የሚቀረፍ በመሆኑ ፈቃዱ በአጭር ጊዜው ውስጥ እንደሚፈቀድና በሚቀጥለው ዓመት ወደ ምርት እንገባለን ብለን እናምናለን" ሲሉ ተናግረዋል ።

ጉጂ ዞን ባቢቹ ቁሊንሱ በሚባል ቦታ ላይ ከተደረገው ጥናት የተገኘው ውጤት አዋጭ በመሆኑ በዚህ ወር ከማኅበራት ጋር በመሆን የሚሠራው ወርቅ ማምረት ሥራ ይጀመራል ያሉት አቶ ሳዲቅ፤ አክለውም እዚያ በጉጂ ዞን በሌላ ሁለተኛ ቦታ ጥናት እየተካሄደ መሆኑን ገልጸዋል። ጥናታቸው የተጠናቀቁ ማዕድናት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መመሪያው ዝግጅት ተጠናቀቆ በሚቀጥለው ዓመት ሥራው እንደሚጀመር ነው ያመላከቱት።

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ የደለል ወርቅ ጊዜያዊ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ሊያልቅ የሚችል ነው። ትልቅ የሚባል ፅንሰ ወርቅ ነው። አሁን ላይ ያለው መረጃ እንደሚያሳየው የደለል ወርቅ በዚህ ደረጃ አለ ማለት ትልቅ ክምችት ያለው ፅንሰ ወርቅ እንዳለ አመላካች ነው። ፅንሰ ወርቅ በጥልቀት በትልቅ ቴክኖሎጂ እና ረጅም ጊዜ (ለ30፣ ለ40 እና ለ50 ዓመታት) የሚፈለግ ነው። ያለው ክምችት ቀላል የሚባል እንዳልሆነና ድንጋዮች ሲመረመሩም ጥሩ ውጤት መኖሩን ጥናቶች አመላክተዋል።

"ፅንሰ ወርቅ ሲባል ቀላል አይደለም፤ በኢትዮጵያ ደረጃም ሊሠራ የሚችል አይደለም። እኛ እነዚህን ውጤቶችና ያለውን ሀብት ይዘን የውጭ ድርጅት ነው የምናፈላልገው። የውጭ ድርጅት ሲመጣ ቴክኖሎጂ፣ መሠረተ ልማት እና በጀት ይዞ ስለሚመጣ ከእነርሱ የሚወሰድ ትልቅ ልምድ አለ። ስለዚህ ፅንሰ ወርቅ ላይ የመጀመሪያ ሥራ እየተሠራ ነው» ብለዋል።

200 ኪሎግራም የሚገመት ወርቅ የተገኘው በትንሽ ቦታ ላይ ነው። ወደፊት ደግሞ ባለው 100 እስኩየር ኪሎሜትር መሬት ላይ ሲሠራ የተሻለ ነገር ይገኛል። ይህ በመንግሥት ደረጃ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ መሆኑን አቶ ሳዲቅ ይገልጻሉ።

«ኮርፖሬሽኑን ከችግር የሚያወጡትና ገቢ የሚያስገኙለት ማዕድናት ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ ነው» ያሉት አቶ ሳዲቅ፤ አሁን ላይ የኮርፖሬሽኑ ትልቁ ገቢ የሚገኘው የኢንዱስትሪ ማዕድን ከሆነው ካኦሊን ምርት መሆኑን ጠቁመው፤ በተለይ የወርቅ ማዕድን ማምረት በጣም አዋጭ እንደሆነ ይገልጻል። በመሆኑ የተጀመሩ ሥራዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል በሚቀጥለው ዓመት ከወርቅ ምርት ጥሩ ውጤቶች ማግኘት እንደሚቻል አስታውቀዋል።

አቶ ሳዲቅ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ብዙ የወርቅ ማዕድን ክምችት ያለባት ቦታ ስትሆን ማዕድን ዘርፉ ላይ ለመሰማራት ብዙ መልካም የሚባሉ ነገሮች አሏት። ከእነዚህ መካከል አንደኛው ጥናት የሚካሄድበት ቦታው ላይ የሚገኘው ድንጋይ የወርቅ ክምችት የሚታይበት መሆኑን ነው። ሁለተኛው ወርቅ ማዕድን ከተገኘ በኋላ በአካል ሆነ በላብራቶሪ የሚፈተሽበት ሁኔታ መኖሩ ነው። በዚህም ኮርፖሬሽኑ በራሱ ላብራቶሪ ማዕድናት እንዲፈተሹ የሚደረጉ መሆናቸው ባለፉት ጊዜያት ከተለያዩ ቦታዎች የተሰበሰቡት ማዕድናት ተመርምረው ጥሩ አመላካች ውጤት ታይቶባቸዋል።

የማዕድን ዘርፉ ከአምስቱ የኢኮኖሚ ምሰሶዎች አንዱ እንዲሆን መደረጉ መንግሥት ለዘርፉ የሰጠውን ትኩረት የሚያሳይ ነው ያሉት አቶ ሳዲቅ፤ ይህ ደግሞ ዘርፉ ትኩረት አግኝቶ አስፈላጊው ሥራ እንዲሠራበት ያስችላል። ኮርፖሬሽኑም በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ስር ትልቅ ገቢን ያመነጫሉ ተብሎ ከተለዩት ዘርፎች መካከል አንዱ ነው። ስለሆነም የቅርብ ክትትልና በፋይናንስ ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ብዙ ሥራ እንዲጠበቅበት ያደርገዋል ብለዋል።

አቶ ሳዲቅ በሀገሪቱ የማዕድን ሀብቱ በብዛት ያለ ቢሆንም እስካሁን ብዙ ያልተሠራበት መሆኑን ይናገራሉ። አሁን ላይ ኮርፖሬሽኑ በዚህ ዘርፍ ያለውን ልምድ ተጠቅሞ አቅሙ፣ ሙያው፣ ካፒታሉ እና የውጭ ትልልቅ ኩባንያዎች ጋር ግንኙነት አጠናክሮ ብዙ ሥራዎች ለመሥራት አቅዶ እየሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

የማዕድን ዘርፉ ብዙ ተግዳሮቶች ያሉበት በተለይ ማዕድናቱ በሚወጣባቸው አካባቢዎች ላይ በእጅጉ ፈታኝና ቢሮክራሲ የሚበዛባቸው ናቸው ያሉት አቶ ሳዲቅ፤ በክልሎች በመንግሥት ዘርፍ ለተሠማሩ ማዕድን አምራች ድርጅቶች ላይ የሚደርሰው ችግር ውስብስብ ስለሆነ ጫናው ይበዛል፤ ችግሮችን በቀላሉ መፍታት አይቻልም ይላሉ። በተጨማሪም በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ በመውሰድ ክልል ሲኬድ ከክልሉ ተፈቅዶ ወረዳ ማዕድኑ በሚገኝበት ቦታው ላይ ለመግባት አላስፈላጊ ጥቅም የሚፈልጉ አንዳንድ አካላት የሚከለክልበት ሁኔታዎች ስላሉ ይህ ደግሞ መንግሥት ለማዕድን ዘርፉ በሰጠው ትኩረት ልክ ለመሥራት አስቸጋሪ ያደርገዋል። በመሆኑም እንደመንግሥት ከላይ ጀምሮ እስከታች ድረስ ብዙ ሥራዎች መሥራት ያለባቸው መሆኑን ገልጸው፤ ኮርፖሬሽኑ በማዕድን ዘርፍ የሚያጋጥሙትን ችግሮች ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሆኖ ሥራዎችን እየሠራ እንደሆነ ያስረዳሉ።

በተመሳሳይ የወርቅ ማዕድን አብዛኛውን ጊዜ የሚገኙበት ቦታ ርቀት ያላቸው ጠረፍ የሚባሉ አካባቢዎች እና አስቸጋሪ ቦታዎች ላይ በመሆኑ ከፀጥታ ጋር የሚያያዙ ችግሮች መኖራቸው ይጠቁማሉ። አሁን ላይ ግን የተሻለ መረጋጋትና ሠላም ስላለ ለማዕድን ሥራው የተሻለ እየሆነ መምጣቱን ገልጸዋል።

ችግሩን ለመፍታት ክልሎች ጋር በመተባበር እነዚህ አካላት ላይ ትኩረት በማድረግ ግንዛቤ እንዲፈጥሩ የሚያደርግ ሥራ በመሥራት ተገቢው ድጋፍና ትብብር እየተደረገ መሆኑን አቶ ሳዲቅ ተናግረዋል። ይህ ሲሆን ደግሞ ወርቁ በትክክል ይመረታል ተመዝኖ በሕጋዊ መንገድ ብሔራዊ ባንክ እንዲገባ እና ሁሉም የአካባቢ ማኅበረሰብ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የኅብረተሰቡን ግንዛቤ በማስፋት ረገድ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ ጠቁመዋል።

የማዕድን ዘርፉ በሕገወጥነት እየተሰፋፋ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ይህን ድርጊት የሚፈጸሙ ግለሰቦችን ወደ ሕጋዊነት ለማምጣት የሚሠሩ ሥራዎች እንዳሉ ሆነው ትልልቅ አቅም ያላቸው ኩባንያዎች እንዲሳተፍ ቢያደርግ የተሻለ ውጤት ማግኘት እንደሚቻል ነው አቶ ሳዲቅ የሚያመላክቱት።

በሌላ በኩል ማዕድን ዘርፉ ከላይ ጀምሮ ድጋፍ እና እገዛ እየተደረገበት መሆኑ ትልቅ አቅም የሚፈጥር መሆኑን ጠቁመው፤ ኮርፖሬሽኑ በማዕድን ዘርፉ ያሉ ተግዳሮቶችን በመፍታት ከክልሎች ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር እየሠራ እንደሚገኝ አንስተዋል። ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር በቅርበት እየሠራ በመሆኑ ለሥራዎቹ እገዛ እያደረገ መሆኑን ጠቅሰዋል። በአጠቃላይ ኮርፖሬሽኑ በማዕድን ዙሪያ በሚሠሩ ሥራዎች ዙሪያ ካሉ አጋርና አጋዥ አካላት ጋር በትብብር መሥራት ሥራዎች በጥሩ ሁኔታ ለመሥራት አስችሏታል ሲል አስገንዘበዋል።

እንደ አቶ ሳዲቅ ማብራሪያ፤ ኮርፖሬሽኑ በሚቀጥለው በጀት ዓመት የያዛቸው ሰፊ ሥራዎች አሉ። የደለል ወርቅ ወደ ማምረት ሥራ የሚገባ ሲሆን፤ ሻኪሶ ባለው ወርክ ሾፕ የወርቅ ማጠቢያ ማሽኖች እየተሠራ ነው። ቢያንስ ሦስት ማጠቢያ ማሽኖችን በመትከል የማልማት ሥራዎች ይሠራሉ። የጽንሰ ወርቅ ጥናት ሥራውን አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። ይህም በጥልቀት የሚቆፈር፣ ብዙ ወጪው የሚጠይቅ እና ከአቅም በላይ ስለሚሆን የውጭ ድርጅት በማፈላለግ የሚሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ጀምበር ግን ታድሳ...

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ኩርፊያ መልክ ቢኖረው ቁርጥ ሩታን ይሆን ነበር። ጠይም ዘለግ ያለ፣ አይኖቹ ከከዋክብት የተዋለዱ የሚመስሉ፣ ጸጉሩን ቁጥርጥር የተሰራ ኩርፊያ ለንቦጩን ጥሎ ካያችሁ አትጠራጠሩ ሩታን ነው። በዳመነ ፊት ከንፈሩን በጥርሱ እየበላ በአንድ የሆነ ቦታ ላይ የመሸገ ፊት ካያችሁ ሩታ ስትሉ ጥሩት አቤት ይላችኋል። ምን እንደሚያስኮርፋት እንጃ..ነው ወይስ አኩርፋ የተፈጠረች ሴት ትሆን?

የጎረቤቴ ሚስት ናት...ያን ሞገድ አፍ ባሏ አድርጋ መኖሯን ሳስብ በሴት ነፍስ እዝነት ይይዘኛል። ብታዩት እኮ ከመጀመሪያው ሰው መሰል እንስሳ ላመል መለስ ቢል ነው። ከጥቁረቱ መልኩ...የሆነ ዳፍንታም። በውበት የሚበልጣቸው...በውበት የሚበልጣቸው ይኖሩ ይሆን? ጦጣና ዝንጀሮ እንደእሱ ሱፍና ከረባት አድርገው አጠገቡ ቢቆሙ አይደርስባቸውም። በዛ ላይ ኩራቱ...መሬት አይንካኝ እኮ ነው የሚለው። ወንድ ምንም ይሁን በቃ ከሴት አለም ሽቶ የሚያጣው የለም ማለት ነው?

ኩርፊያ አይወድም መሰለኝ ባኮረፈች ማግስት ድራሽ አባቱ ይጠፋል። ጠዋት የወጣ ማታ ነው ቤት የሚመለሰው። ያ ወጥቶ የሚመለስበት ጊዜ ለእኔ በአይነቱ የተለየ ለመቼም የማይዘነጋ ትውስታዬ ነው። ሰው መቼም ካለአንድ አመል አይፈጠር የእሷ ኩርፊያ የእሱ መመነኛ ለእኔ ደግሞ የእግዚአታ ደብሬ ነው። በድሎት ከማነሳቸው በጎ ገጠመኞቼ መሀል ይሄኛው በሁለት መልኩ ይለያል። የመጀመሪያው በሚስቱ ኩርፊያ ሚስቱን ለማንም ትቶ መሄጃውን የሚሰውር ባል መኖሩ፣ ሌላኛው በባሏ መሄድ ጎረቤቷ ደረት ላይ በምትጽናና ሴት ነው። መቼም ይሄ እድል የእናንተ ቢሆን ቢብስ እንጂ አያንስም።

ሲያስኮርፋት ብን ወደእኔ...እኔም ያለስስት ደረቴን ስጥት። አይኗን ከድና ለጥ ደረቴ ላይ። ገርበብ ያለውን በር መለስ አደርግና በጠባቧ ቤቴ ውስጥ ውብ ሴት ያለችበትን ህልም አልማለው። በዚህ ጊዜም ሆነ ባለፈውና በሚመጣው ጊዜ ውስጥ እንደእኔ ቤት እድል የገጠመው ማነው? በእጆቼ ጸጉሯን እየደባበስኩ እስክትሸር እሽሩሩ እላታለው። የነፍሴን ትርታ እንደማጀቢያ ሙዚቃ ተጠቅሜ፣ በዛ ጅላጅል ባሏ የተሰጠኝን ነጻ ስጦታ እያጣጣምኩ፣ የሆነውንና እየሆነ ያለውን ባለማመን ነፍሴን አርዳለው። አንዳንድ ከእለታት ውስጥ የሚበቅሉ ይሄን መሳይ በእውን ሆነው ህልም የሆኑ ያህል የሚሰሙን ታሪኮች ይበቅሉብናል። ባለጊዜ ሆኜ ለዚህ ክብር ስታጭ አለም ጠበበችኝ። ድንቄም ክብር! አለኝ ውስጤ። የሰው ሚስት ማማገጥ ምኑ ነው ክብር? ላለኝ ውስጤ ‹መጣችብኝ እንጂ አልሄድኩባት ደግሞስ ደረቴን በነጻ ለመጽናኛ መስጠቴ ምኑ ነው ክፉ? ስል አንገት አስደፋሁት።

ወደሥራ ልወጣ በተሰናዳሁበት እና ሁሉ ነገሬን ጨርሼ ስከርቤን አንገቴ ላይ መጣል ብቻ በቀረኝ ማክሰኞ ጠዋት ላይ እንደልማዷ አኩርፋ ወደቤቴ ስተት አለች። ጠዋት በሆነች ውብ ሴት ኩርፊያና ውበት ስር ምን እንደሚመስል የሚያውቅ ያውቀዋል። ደረቴን ሰጠኋት ወደቀችበት። የባሏ ኮቴ ከውጪው በር ደርሶ በሩን በኃይል ወርውሮ ሲያጋጨው የተሰማው ድምጽ እንደወጣ ቢቀር፣ መኪና ቢበላው፣ የሆነ ጥጋበኛ ማጅራቱን ብሎት ማታ መርዶው በመጣ የሚል እርግማን እንዳወርድበት አደረገኝ። ይሄን ያክል ምን አስጨከነኝ? ለምን ጠላሁት? ራሴን ታዘብኩት።

በባሏ እልህ ይሆን እንጃ ያኮረፈ ፊቷን ከደረቴ ላይ ፈንቅዬ ፊት ለፊቴ አቆምኩት። የብርሀን ግት የሚመስል ኩርፊያ ፊቴ ላይ ዘነበ። ግቱ ሲፈርጥ አራስ ብርሃናት እንደጎርፍ ካፊያ ላዩ ላይ አካፉ። ለዘላለም እንዲያ ሆናና ሆኜ ብንኖር..ተፈጥሮ ለአንድ ጊዜ ተፋልሶ እኔና እሷን በቆምንበት እንዳለንበት ቢረሳን...ቢተወን። እንደእሷ ኩርፊያ ምን የጣፈጠ ቀምሻለው? ምን የጣመ በልቻለው? በልጅነቴ የእናቴ ጡት፣ በአፍላነት የመከሊት ፍቅር፣ በወጣትነቴ ደግሞ የእሷ ኩርፊያ የታሪኬ ሰንበር ሆነው እስከማብቂያዬ ይከተሉኛል።

ኩርፊያዋ የውበቷ ካባ ነው...የሴትነቷ መውዜር። የነፍሷ ነፍስ፣ የአካሏ ጥላ...ተፈጥሮ በውብ ሽምኖ ያለበሳት ቡሉኮ። የአንዳንድ ነፍስ ኩርፊያ እንደታቦት ማደሪያ መንፈስ ቅዱስ የጸለለበት ነው። ከዓለም ውበቶች የሚበልጠውን ይዘው ለፍቅር አበሜኔት የታጩ። ገነት በአንዳንድ ፊቶች ኩርፊያ ጥላ ስር ያለች ትሆን? አልደረስ ያሉ ህልቆ መሳፍር መሻቶች በውብ ሴት ኩርፊያ ጀርባ ያሉ ይሆኑ? እንጃ ብቻ ስታኮርፍና ከማውቀው ነባር ሴትነቷ ስትሸሽ አብራ ወደሆነ የከፍታ ምኩራፍ ታሸሽኛለች። ከነኩርፊያዋ ደረቴ ላይ ተጋድማ ሳያት ገነት ከስረ መሰረቷ ደረቴ ላይ የተገነደሰችብኝ ይመስለኛል። ገነትን የማባብል፣ መንግስተ ሰማያትን የምደባብስ ይመስለኛል።

ያኮረፈ ፊቷን ፊት ለፊቴ አቁሜ ‹ጀምበር ግን ታድላ ሁለት ሀገር አላት...ወጥቶ መግቢያዋ ሁለት ነው› አልኳት በራፌን ጥሳ በገባችው የጠዋት ጀምበር ወሬ እየጀመርኩ።

እንዳልገባው በመሆን ፊቴ ላይ ስትምነሸነሽ... ‹በምሥራቅ ጠፍ ስር ተጸንሳ፣ በምድር ወገብ ላይ ብራምባሯን ሰብራ፣ በምዕራብ በኩል ደህና እደሩ ትላለች›። ስል ተነተንኩላት። እያደመጠችኝ እንደሆነ ሳውቅ ‹ምዕራብ መሞቻዋ ይሆን? ከሆነ ደግሞ በምሥራቅ ብቅ አትልም ነበር› ስል ቀላመድኩ።

ፈገግ አለችልኝ። በኩርፊያ ውስጥ ፈገግታ ምን እንደሚመስል ለማየት የታደልኩት እኔ ሳልሆን አልቀርም። በኩርፊያ ውስጥ ፈገግታ እንዲያ መሳይ እንደሆነ አላውቅም ነበር። የእውነት በኩርፊያ ላይ ፈገግታ እንደተሲያት ጥላና እንደ ክረምት ጣይ ልዩ ስሜትን የሚፈጥር ክዋኔ ነው። ጣና ዳር ተቀምጦ ከደማቅ የብርሀን ትውከት ጋር የጀምበርን መሰወር ከማየት ጋር መሳይ ነው። ከሆነ ስሜት ጋር ወደጀምበር መውጫ ሀገር ኮበለልኩ..። ምሥራቅ አድማስ ፀሐይን ሊወልድ ሲያምጥ፣ የምድር ወገብ አራስ ጥየቃ ነጠላ ሲያገድም፣ ምዕራብ በበኩሉ ቄጠማ ሲጎዘጉዝ አለምኩ። አኩራፊዋ ሴት ወደደረቴ ስትከጅል ሊያዘነብል ባለው የጭንቅላቷ ጥላ ታዘብኩ። ከጅላም አልቀረች ትንፋሻችን ተቀላቅሎ በአንድ ሳንባና ጉሮሮ የምንተነፍስ እስኪመስል ድረስ ተጠጋችኝ..። ከደረቴ ዝቅ ብሎ ያለው ቦታ ላይ የጡቶቿ ቀንድ ሲጭረኝ ይታወቀኛል። አንገቴ ግድም የተወችው ሰንፋጭ መዐዛዋ ያናውዘኛል። ደረቴ የአንድ ጎን ምስሏን አትሞ ከወንድነቴ አቆራኝቷታል። ወገቤ ግድም እጇን ተወናግሮ ሳየው የምናገረው አጣሁ። አመጣጧ ለማረፍ እንዳይደለ ገባኝ። ከንፈሯ ደርቆ፣ ውብ ፊቷ ጠውልጎ ሳያት ደግሞ ከባሏ ሽሽት እኔ ቤት መምጣቷ እና ደግሞ እዚህ ደረት ላይ ምን ፈልጋ እንደምትወድቅ እየገባኝ መጣ። ቀርፋፋ ነኝ መቸኮል አልችልበትም። በእንቁርስሴ ብዙ የባከኑ እድሎች አሉኝ። በጓደኞቼ ዘንድ እድሎቼን ባለመጠቀም እታወቃለሁ...።

ባለማፈር፣ ከየት እንደመጣ በማላውቀው ድፍረት ከንፈሯ ላይ ሰነበትኩ..በደንብ አየኋት። አይን ለአይን መተያየት ያለው የሞገድ ኃይል እንደዛ ነው? መተያየት ያን ያክል የኤሌክትሪክ ሜጋ ዋት እንደተሸከመና ከመነካካትና ከመዳራት እኩል ስሜት ያለው ተፈጥሮ እንደሆነ አለማወቄ ከሴት የተገለልኩ እንደሆንኩ እንዳስብ ከማድረግ ባለፈ ከዛን መሳይ ስሜት መራቄ ቁጭትን ፈጠረብኝ። በዚህ ቀን ላይ በዚች ሴት ታሪኬን ለመቀየር ስል ይሆን አላውቅም ከዓለም ደፋሩን ሴት አውል ሆኘ አይኗ ስር ተገኘሁ። ውብ ናት...ሁሉም ሰው በእኩል የሚስማማበት ውበት አላት። ለውበቷ ድምቀት የሆነ የፊቷን አንድ ሦስተኛ የያዘ አይን አላት። ማንም ስለእሷ እርግጠኛ ሆኖ ከሚናገረው ውስጥ አንዱ የአይኗ ውበት እና ሌላው ደግሞ በኩርፊያ ውስጥ የሚገዝፍ ቁንጅናዋ ነው። ለሁለቱም መመረጤን ሳስብ ከወንድ እኔ እንደገና ከወንድ ያ ለንቦጫም ኩታራ ባሏ የፍቅር ጀብደኞች መሆናችን መጣብኝ። ፍቅርሽ የምሞትለት አላማዬ ነው፣ ነፍሴ ግዛቷ አድርጋሽ ሰንደቅሽን ተክላለች፣ የትኛውም ምድራዊ ኃይል ከአንቺ አያርቀኝም› ልላት ከአፌ ላይ መለስኩት..። የሰው ሚስት እንዲህ ትባላለች? ወደድኩህ አላለችኝ...ኩርፊያዋን በደረቴ ለመሻር ተጠጋችኝ እንጂ!

በትንፋሷ እየሞቅኩ ወገቤ ላይ ተጣብቃኝ ሳገኛት የሆነ ድፍረት ወደከንፈሯ እንድንደረደር አስገደደኝ...። ላድርገው አላድርገው ስል አመት የሰነበትኩ ይመስለኛል.. በስተመጨረሻ...

# ዓለም አቀፍ

## ሩሲያና ሰሜን ኮሪያ አንዳቸው ለሌላኛቸው ሁሉንም አይነት ወታደራዊ ድጋፍ ለማድረግ ስምምነት ላይ ደረሱ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሰሜን ኮሪያ እና ሩሲያ ከሁለቱ በአንደኛቸው ላይ ወታደራዊ ጥቃት በሚቃጣበት ወቅት ወታደራዊ ድጋፍ ለማቅረብ የሀገራቱ መሪዎች ስምምነት ላይ ደርሰዋል።

ይህ ስምምነት የተደረሰው የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ከ24 ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በሰሜን ኮሪያ ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት ነው።

ስምምነቱ ሁለቱ የቀዝቃዛው ጦርነት አጋሮች በፈረንጆች 1961 ተፈራርመውት የነበረው እና ሶቭየት ህብረት ከደቡብ ኮሪያ ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ስትጀምር ተሰርዞ የነበረውን ወታደራዊ ትብብር የሚያድስ ነው ተብሏል።

“ኮምፕርሄንሲቭ ስትራቴጂክ ፓርትነርሺፕ” ለማድረግ በሩሲያው ፕሬዚዳንት ፑቲን እና በሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን መካከል ከትናንት በስቲያ የተደረሰው ስምምነት ሞስኮ በዓመታት ውስጥ በእስያ አህጉር ያደረገችው ትልቅ እርምጃ ነው።

“ከሁለቱ በአንደኛቸው ላይ ጦርነት የሚታወጅ ከሆነ ወይም በጦርነት ውስጥ ካለ፣ በተመድ ቻርተር አንቀጽ 54 መሰረት ሌላኛው ሁሉንም አይነት ወታደራዊ እና ሌሎች ድጋፎችን ወዲያውኑ ያቀርባል” ይላል የስምምነቱ አንቀጽ አራት።

የተመድ ቻርተር አንቀጽ 51 አባል ሀገራት ወረራ ሲፈጸምባቸው በተናጠል ወይም በቡድን ራሳቸውን መከላከል እንደሚችሉ ያስቀምጣል።

ስምምነቱ ሩሲያ በዚህ ምዕተ ዓመት የኑክሌር ጦር መሳሪያ የሞከረችውን ሰሜን ኮሪያን ምን ያህል ልትረዳት ትችላለች የሚል ምዕራባውያንን ስጋት ውስጥ ከቷቸዋል።

ኪም የበላይነት እና ኢምፔሪያሊዝምን ለማስቀጠል የሚጥረውን የምዕራባውያን ፖሊሲ እንዋጋለን የሚለውን የፑቲን መግለጫ አስተጋብተዋል።

ሁለቱ ሀገራት አንዳቸው የሌላኛቸውን ጥቅም የሚጻረር ስምምነት ከሦስተኛ ሀገር ጋር እንዳይፈራረሙ እና ግዛታቸውንም ደህንነት እና ሉአላዊነት ለሚጎዳ ሌላ ሀገር ላለማስጠቀምም



ተስማምተዋል ተብሏል።

በተጨማሪም የቀጣናውን ብሎም ዓለምአቀፍ ሰላምን ለማስፈን ወታደራዊ አቅማቸውን ለማጠናከር የሚያስችሉ ርምጃዎችን ይወስዳሉ።

ፕሬዚዳንት ፑቲን፣ ሩሲያ በዩክሬን ለምታካሂደው ወታደራዊ ዘመቻ ሙሉ ድጋፍ የሰጠችውን ሰሜን ኮሪያን አመስግነዋል።

ጃፓን ሩሲያ ከሰሜን ኮሪያ ጋር ያላት ትብብር እንደሚያሰጋት ገልጻለች።

ከሰሜን ኮሪያ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚ ዋና ተጠቃሚ የሆነችው ቻይና በሁለቱ ሀገራት ግንኙነት ጉዳይ ምንም ማለት አልፈለገችም።

ዋሽንግተን እና ሴኡል ግን እየጠነከረ የመጣው የሩሲያ እና ሰሜን ኮሪያ ግንኙነት ስጋት ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል።

ምዕራባውያን ሰሜን ኮሪያ ሩሲያ በዩክሬን ለምታደርገው ጦርነት ጥቅም ላይ የሚውል የጦር መሳሪያ ታቀርባለች ሲሉ ይከሷታል። ሰሜን ኮሪያ ግን የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ነው ስትል አስተባብላለች።

## ቦይንግ ኩባንያ 25 ቢሊዮን ዶላር እንዲቀጣ የአደጋው ሰለባ ቤተሰቦች ጠየቁ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የቦይንግ ኩባንያ 25 ቢሊዮን ዶላር እንዲቀጣ የአደጋው ሰለባ ቤተሰቦች መጠየቃቸው ተገለጸ።

በሁለት የቦይንግ 737 ማክስ አውሮፕላኖች አደጋ ሕይወታቸውን ያጡ ሰለባዎች ቤተሰቦች በአሜሪካ ታሪክ ከባድ ለተባለው ኮርፖሬት ክራይም” 24 ነጥብ 8 ቢሊዮን ቅጣት እንዲጣል እና ክስ እንዲመሰረት መጠየቃቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ቦይንግ በፈጸመው ወንጀል የደረሰው የሞት መጠን ከባድ በመሆኑ መጠኑ “ምክንያታዊ እና ተገቢ ነው” ብሏል የቤተሰቦቹ ጠበቃ ፓውል ካሴል።

ቢቢሲ እንደገለጸው፤ ካሴል ባቀረበው ባለ 32 ገጽ ደብዳቤ በ2018 እና በ2019 በደረሱ ሁለት የመከስከስ አደጋዎች 346 ሰዎች በሞቱበት ወቅት ኩባንያውን ሲመሩ የነበሩ ሰዎች መከሰስ አለባቸው ብሏል።

ይህ ደብዳቤ የቦይንግ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዴቭ ካልሆን ባለፈው ማክሰኞ እለት በኮንግረስ ፊት ቀርበው ይቅርታ መጠየቃቸውን ጠቅሷል።

“ላደረስነው ጉዳት ይቅርታ እጠይቃለሁ” ሲሉ የሰለባዎቹ ቤተሰቦች በጩኸት ንግግራቸውን አቋርጠዋቸዋል ተብሏል።

ሁለቱ የቦይንግ 737 ማክስ አውሮፕላን አደጋ የደረሰባቸው በተለያየ ጊዜ ቢሆንም የአደጋው መንስኤ ግን ተመሳሳይ ነበር።

በፈረንጆቹ ጥር 2018 ንብረትነቱ የላዮን ኤየር ፍላይት የሆነ አውሮፕላን ከኢንዶኔዥያ ዋና ከተማ ጃከርታ ከተነሳ ከ13 ደቂቃ በኋላ ባጋጠመው የመከስከስ አደጋ ተሳፍረው የነበሩ 189 ሰዎች ሕይወታቸው አልፏል።

በመጋቢት 2019 ደግሞ ንብረትነቱ የኢትዮጵያ አየርመንገድ የሆነ ቦይንግ 737 ማክስ አውሮፕላን ከቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ከተነሳ ከስድስት ደቂቃ በኋላ ሲከሰከስ አሳፍሯቸው የነበሩት 157 ሰዎች ሞተዋል። በሁለቱም አደጋዎች በሕይወት የተረፈ ሰው የለም።

ሁለቱም አደጋዎች በበረራ መቆጣጠሪያ ሥርዓት ብልሽት ምክንያት ነበር የተከሰቱት።

ኮልሆን ኮንግረስ በቀረቡበት ወቅት ኩባንያው ስህተት መሥራቱን አምነው እና ከስተቱ ተምሯል ብለዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው ቦይንግን ምስጢር በማያወጡ ግለሰቦች ላይ እርምጃ መውሰዱን ገልጾ የሠራተኞቹን ስጋት ግን እንደሚያዳምጥ ተናግረዋል።

የአሜሪካ የፍትህ ክፍል ወይም ጀስቲስ ዲፓርትመንት ከሁለት



የመከስከስ አደጋዎች ጋር በተያያዘ በቦይንግ ላይ በፈረንጆች 2021 ጀምሮ የነበረውን የወንጀል ክስ እንደገና ለመጀመር እያጤነው ነው።

ክስ የቆመው ኩባንያው የአየር ተቆጣጣሪዎችን ማሳሳቱን ካመነ እና ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች የሚቆጣጠር አዲስ ኮምፒሊያንስ ሥርዓት ለመዘርጋት ቃል መግባቱን ተከትሎ ነበር።

ባለፈው ወር በረራ ላይ የነበረ 737 ማክስ አውሮፕላን በሩ ከተገነጠለ በኋላ አቃቤ ሕግ ቦይንግ ስምምነቱን ጥሷል የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል።

ጀስቲስ ዲፓርትመንት እስከ ፈረንጆቹ ሐምሌ ሰባት ድረስ ክሱ እንደገና ይጀመር ወይስ አይጀመር በሚለው ጉዳይ ውሳኔ ይሰጣል።

ካሴል ደንበኞቻቸው ወይም የአደጋ ሰለባ ቤተሰቦች በቦይንግ ላይ ወደፊት ከሚጣለው ቅጣት ላይ የተወሰነው የኩባንያውን ደህንነት እና የጥንቃቄ አሠራሮች የሚቆጣጠር ነጻ ተቆጣጣሪ ለማቋቋም እንዲውል ሃሳብ ማቅረባቸውን ገልጸዋል።

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# የኢትዮጵያውያንን የመረዳዳት እሴት እያጎለበተ የመጣው በጎ ፈቃደኝነት

**በኃይሉ አበራ**

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ አካባቢዎች ተግባራዊ መሆን ከጀመረ የቆየ ቢሆንም፤ በመደበኛነት ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ በመዲናዋ በተለያዩ መርሐ ግብሮች በወጣቶች ሲተገበር መቆየቱን መረጃዎች ያመላክታሉ።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ በተለያዩ ምክንያቶች ተቀዛቅዞ የቆየውን የኢትዮጵያውያንን የጋራ እሴት በማነቃቃት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያበረከተ ነው፡፡ በዚህ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በርካታ ዜጎች ያዘመመ ቤታቸው ቀና እንዲል ሆኗል፤ ተማሪዎች ለቀጣዩ ትምህርት ተዘጋጅተውበታል፤ ለአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር መሳካት ትልቅ አበርክቶ በማድረግ የችግኝ ተከላና ሌሎች በርካታ ተግባሮች ተከናውነውበታል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ እየጎለበተ የመጣው የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት አሁን አሁን ደግሞ ወደ ሀገራዊ እንቅስቃሴ አድጓል። ዘንድሮም በመላ ሀገሪቱ የሚካሄደው የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰሞኑን ይፋ ተደርጓል፡፡

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያውያን አብረው በመብላት ብቻ ሳይሆን አብረው በመሥራት፣ በጎና መልካም በማድረግ፣ አዛውንቶችን በማክበር፣ ያለው የሌለውን በመደገፍ ይታወቃሉ፤ ይህን ማድረግ ለዘመናት የቆየ የጋራ እሴታቸው ነው። በተለይም 98 በመቶው ሕዝብ አማኝ መሆኑ የሚነገርላት ኢትዮጵያ በክርስትናውና በእስልምናው እንዲሁም በተለያዩ እምነቶችና መልካም እሴቶች የተቀረፁ ናቸው፡፡

ከዚህ የበጎነት እሴቶቻቸው ከመነጩትና በተለይ በመዲናዋ አዲስ አበባ በስፋት ተግባራዊ እየሆኑ ከሚገኙት የበጎነት ሥራዎች አንዱ የአቅመ ደካሞች ቤት እድሳት ነው። በዚህ የቤት እድሳት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ /ዶ/ር/ እንዲሁም ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ጨምሮ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ በዚህ የበጎ ተግባር ከተከናወኑ ተግባሮች መካከል የመኖሪያ ቤት እድሳት አንዱ ነው፡፡ ብዙ ሺ አቅመ ደካሞችና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች የመኖሪያ ቤታቸው ታድሶላቸዋል፡፡ በርካቶችም አዳዲስ ዘመናዊ ባለብዙ ወለል መኖሪያ ቤቶች ተገንብተውላቸዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዋ የ85 ዓመቷ ወይዘሮ ዓለምነሽ ባሩዳ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የመኖሪያ ቤቶች እድሳት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ የመኖሪያ ቤት እድሳቱ የተደረገላቸው በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስተባባሪነት እና በበጎ ፍቃደኛ ባለሀብቶች ድጋፍ ነው፡፡

ከንጉሡ ዘመን ጀምሮ ቤተሰብ አፍርተው በራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ በአሮጌ የቀበሌ ቤት ውስጥ የኖሩት ወይዘሮ አለምነሽ፣ የአንድ ሴት እና አንድ ወንድ ልጅ እናት ናቸው፡ ከወለዷቸው ልጆች በተጨማሪ አምስት ያሳደጓቸው ልጆች እንዲሁም እሳቸው በድምሩ ስምንት ቤተሰብ ሆነው ባዘመመ ጎጇቸው ይኖሩ ነበር፡፡

ይሁንና ወይዘሮ አለምነሽ ቤታቸው ስለታደሰላቸው በእጅጉ ተደስተዋል፤ አሮጌውን ከጭቃ የተሠራ የቀበሌ ቤት አድሶ፣ አሳምሮ እንዲገቡበት ያደረጉላቸውን ወገኖች ሁሉ አመስግነው መጨረስ አልቻሉም፡፡ የቀድሞውን ቤታቸውን መፀዳጃ ቤት መንግሥት እንዳሠራላቸው አስታውሰው፣ ማዕድቤት እና አጥሩን ደግሞ በራሳቸው ሠርተው ይኖሩበት እንደነበር ይገልጻሉ፡፡ አሮጌውን ቤት በማፍረስ የተሻለ ቤት እንዲገነባላቸው ሲጠየቁ በእጅጉ ተደስተው የሀሳቡን አቅራቢዎች መርቀዋል፡፡

አሁን በታደሰው ቤታቸው እየኖሩ የሚገኙት ወይዘሮ አለምነሽ፣ የመንግሥት ባለሥልጣን እና አስተዳዳሪዎች፣ የሚኖሩበት ወረዳ መምህራን፣ ባለሀብት እና በጎ ፈቃደኞች ወጥተው፣ ወርደው፣ አቅመ ደካሞቹ ቤት ፈርሶባቸው፣ ጣሪያ አፍሶባቸው፣ በምን ላድስ፣ በምን ልሥራ ብለው ሲጨነቁ እንደ ፈጥኖ ደራሽ ደርሰው እከሌ ትልቅ ነው እከሌ ትንሽ ነው ሳይሉ ለሁሉም የዚህ አይነት ቤት ሠርተው በአጭር ጊዜ ውስጥ አስረክበዋል ሲሉም በቤት እድሳቱ የታየውን ርብርብና የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል። የታደሰውን ቤት "እንደሰጡን ሁሉ ፈጣሪ አብልጦ ይስጣቸው፣ ወንበራቸው ከፍ ይበል" ብለው መርቀው እንደገቡበትም አስታውሰዋል።

> **ኢትዮጵያውያን አብረው በመብላት ብቻ ሳይሆን አብረው በመሥራት፣ በጎና መልካም በማድረግ፣ አዛውንቶችን በማክበር፣ ያለው የሌለውን በመደገፍ ይታወቃሉ፤ ይህን ማድረግ ለዘመናት የቆየ የጋራ እሴታቸው ነው**

በቀድሞው ቤታቸው እያሉ የዛሬ 20 ዓመት አካባቢ ወድቀው ታመው እንደነበር አስታውሰው፣ ከእድሜ መግፋት ጋር ተያይዞ የጤና ችግሮች እንዳሉ ነግረውናል። ታድሶ በተሰጣቸው የምድር ቤት ምንም ሳይቸገሩ በምርኩዝ እየተንቀሳቀሱ እንደሚገኙና ከጤናም አኳያ ጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳሉ ይገልጻሉ።

በራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ በአዲስ አበባ ቤቶች ኮርፖሬሽን የቤት እድሳት ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል የ70 ዓመት አዛውንት ወይዘሮ ፅጌ ረጋሳ አንዷ ናቸው። ወይዘሮ ጽጌ ከደርግ ጊዜ ጀምሮ በአካባቢው ለበርካታ ዓመታት ኖረዋል፡፡ የቀድሞው የቀበሌ ቤታቸው የመፀዳጃ ቤቱ የሕዝብ ነበር፡፡ 14 ቤተሰብ ጋር የሚጠቀሙበትና ምቹ ያልነበረ ነው። ውሃም በጋራ ይጠቀሙ ነበር።

የአስም እና የደም ብዛት ታማሚ መሆናቸውን የገለጹት ወይዘሮ ፅጌ፣ ባለፈው ክረምት የቀድሞው የጭቃ ቤታቸው በአዲስ መልኩ መገንባት ሲጀመር፣ ቤተመንግሥት በሚባለው ትምህርት ቤት ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ መቆየታቸውን ይገልጻሉ፡፡ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ሲገቡም እሳቸውም ቅድስት ማሪያም ፊትለፊት አካባቢ በጊዜያዊነት ቆይተዋል።

የቤቱ እድሳት ተጠናቆም ባለ ሁለት መኝታ ቤት ውስጥ ለመኖር በቅተዋል። ውሃ ለሁሉም ቤት መግባቱን፣ የመፀዳጃ ችግር መቀረፉን፣ የእቃ ማጠቢያ ለብቻ እንዳላቸውም አስታውቀዋል፡፡ በአዲሱ ቤት እስከ አሁን መብራት እንዳልገባም ጠቅሰው፣ ከጎረቤት መብራት ለመሳብ ሦስት ሺህ ያህል ብር አውጥተው ገመድ መግዛታቸውን ጠቁመዋል፡፡ መብራት እንዲገባላቸውም ጠይቀዋል።

በሀገራችን የእነወይዘሮ ዓለምነሽ ባሩዳን አይነት የበጎ ሥራ የተሠራላቸው አቅመ ደካሞች እጅግ በርካታ ናቸው፡፡ በተለይ በአዲስ አበባ በርካታ ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤት እድሳት ተደርጎላቸዋል፤ ሌሎች በርካታ የሚሆኑም ቤታቸው በአዲስ መልክ ተገንብቶላቸዋል፡፡ ባለብዙ ወለል መኖሪያ ቤቶች ተገንብተው ለእነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተላልፈዋል፡፡ በበጎ አድራጎት ተግባር ሌሎች በርካታ አገልግሎቶችም ተሰጥተዋል፤ እየተሰጡም ይገኛሉ፡፡ አገልግሎቱ በመላ አገሪቱ እንዲስፋፋ እየተሠራ ነው፡፡

በዘንድሮው የክረምት ወቅትም አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስችሉ መርሐ ግብሮች ሰሞኑን ተካሂደዋል፡፡ የዘንድሮው አገር አቀፍ የክረምት ወራት በጎ ፈቃድ የማኅበረሰብ አገልግሎት 40 ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጐች እንደሚሳተፉ መርሐ ግብሩን አስመልክቶ ሰሞኑን መግለጫ የሰጡት የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የሠላም ሚኒስቴርና ትምህርት ሚኒስቴር አስታውቀዋል፡፡

የየሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶቹ ሚኒስትር ዴኤታዎች ሀገር አቀፍ የክረምት ወራት በጐ ፈቃድ የንቅናቄ መርሐ ግብርን አስመልክተው በሰጡት የጋራ መግለጫ እንዳስታወቁት፤ የዘንድሮው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ማስጀመሪያ መርሐግብር "በጐነትና አብሮነት ለኢትዮጵያ ከፍታ" በሚል መሪ ቃል ይካሄዳል፡፡ በዚህም 50 ሚሊዮን ዜጎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል።

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሙና አሕመድ በዚህ ወቅት እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያ በበጐ ፈቃድ አገልግሎት የረጅም ጊዜ ታሪክ ያላት ሀገር ስትሆን፣ በተለይ ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎቱ በመደበኛ ሁኔታ ተጠናክሮ ቀጥሏል። ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ ለአገልግሎቱ በተሰጠው ትኩረትም የበጐ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪ ዜጐች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይገኛል።

ወይዘሮ ሙና እንደተናገሩት፤ በዘንድሮው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ተቋማዊ ቅንጅት በመፍጠር ውጤታማ ሥራ ለማከናወንና የሕዝብን የላቀ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ታቅዷል። በተለይም ብሔራዊ የወጣቶች የዜግነት አገልግሎት የሚባል አዲስ አዋጅ እየተዘጋጀ ነው። ይህም አገልግሎት እድሜያቸው ከ18 እስከ 35 ዓመት የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ብቻ የሚሳተፉበት ነው። ወጣቶች የሀገር ፍቅር ስሜት እንዲኖራቸው፣ ማገልገል ክብር መሆኑን እንዲያስቡ እና ስብዕናቸው የተገነባ እንዲሆን የሚያግዝ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ የቀረበ መሆኑን አንስተዋል።

የሠላም ሚኒስትር ዴኤታ ከይረዲን ተዘራ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ሀገራችን ዘመናትን የተሻገረ ታሪክ ያላት ብትሆንም፣ ያንን የሚመጥን የፖለቲካ ባሕል አልነበረም፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት አንዱ መሣሪያ የቆየውን የአብሮነት እሴት ማሳደግ ነው።

የበጐ ፈቃድ አገልግሎቱ ማኅበራዊ ትስስርን ለማጠናከርና ነባር የአብሮነት እሴትን ለማደስ ትልቅ ሚና አለው። ኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀገር እንደመሆኗ ውስጥ የተለመደ የአብሮነት እሴት አላት። ይህንን ማምጣት እና በተለይ ዘመናዊ በሆነ መልኩ ለሀገረ-መንግሥት ግንባታ እና ለሀገራዊ አንድነት መጠቀም ይገባል።

ወጣቱ አሁን ባሕል አለው፣ በርካታ የአዛውንት ቤቶች እየታደሱ ነው። በቀደምት ጊዜያት በኢትዮጵያ ታሪክ የመንግሥት እና የማኅበረሰብ ተራክቦ ሻክሮ ቆይቷል። አሁን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ወጣቶች በትምህርት ቤቶች እየተመገቡ ናቸው። በማኅበረሰቡ ውስጥ በሕዝብ ውስጥ ያደገና የተማረ ወጣት ለሀገሩ ታማኝ ይሆናል ሲሉ ከይረዲን (ዶ/ር) አብራርተው፣ ይህ የክረምት ሀገራዊ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ንቅናቄም ወጣት ብቻ ሳይሆን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚሳተፍበት ሰፊ ሀገራዊ ፋይዳ እንዳለው አስገንዝበዋል።

በአገልግሎቱ ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በመሄድ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ዝግጁ መሆናቸው የተገለጸ ሲሆን፣ በዚህም በመላ ሀገሪቱ 20 ሺ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ለአገልግሎቱ እንደሚሠማሩ ተጠቁሟል፡፡ ለተማሪዎቹም የአንድ ሳምንት ሥልጠና እየተሰጣቸው ይገኛል፡፡

ሥልጠናውም የሀገር መሠረታውያን በሚባሉት በሀገራዊ ማንነት፣ በሀገራዊ ጥቅም እና በሀገራዊ የጋራ እሴቶች ላይ ያተኮረ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ አንድን ሀገር የሚያቆም ካስማና ማገር የሆኑ በተለይ በሀገራችን አሉ የተባሉ ሀገራዊ እሴቶቻችን በጥናት የተሰነዱ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በእነዚህ ላይ ሥልጠናዎች ይሰጣሉ ብለዋል።

ወጣቶቹ ከበጎ ተግባር ሥራዎቻቸው ጎን ለጎንም ሀገራቸውንና እሴቶቻቸውን አውቀው ሀገራዊ መብቶቻቸውን አጠናክረው ሁሉም የሁሉም አካል መሆናቸውን አውቀው ከተወለዱበት አካባቢ ውጭ በሌላ ክልል እንደሚሰማሩም አመልክተዋል።

በጎነት እና አብሮነት ዞሮ ዞሮ ከፍ አድርጎ ማሳየት ነው ያሉት ከይረዲን (ዶ/ር)፣ እነዚህ ሁሉ ተደማምረው ሲሄዱ እዚህም እዛም የሚታዩ የሠላም እጦቶች ተደራሽ የሚደረጉበት አንዱ አቅም መሆኑን አመላክተዋል።

በሀገራችን አብዛኛው አካባቢዎች በእምነታቻው የሚታወቁ ጠንካራ ባሕል ያላቸው፣ የሚረዳዱ ካለው የሌለውንም የሚያካፍሉ ናቸው። የትኛውም አካባቢ ያሉ ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው ያሉብንን ችግሮች በአብሮነት የምንፈታቸው ናቸው። የሚያጋጩን ችግሮችም ከሚፈቱበት መንገዶች አንዱ አብሮነት፣ መደጋገፍ፣ ኢትዮጵያዊ የጋራ እሴት ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ /ዶ/ር/ ያስጀመሩት የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ንቅናቄው በመላው የሀገሪቱ አካባቢዎች ይከናወናል። የኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት በሙሉ የዚህ የበጎነት ማስፈፀሚያ ወሰን መሆኑንም ጠቁመዋል።

የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ኮራ ጡሽኔ በበኩላቸው እንደገለጹት፣ የበጐ ፈቃድ አገልግሎቱ እየተሸረሸረ የመጣውን የአገሪቱን የአብሮነት እሴት ለማደስ አይነተኛ ሚና ይኖረዋል። በንቅናቄው የትምህርት ሚኒስቴር 20 ሺህ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን በወሰን ተሻጋሪ የበጐ ፈቃድ አገልግሎት ያሳትፋል።

ተማሪው ሀገር ውስጥ ያለውን እምቅ አቅም ሲረዳ የሌላውን ባሕል እና ቋንቋ፣ አኗኗር ሲያውቅ የሀገሪቱን ችግሮች እና ፈተናዎች፣ መልካም ዕድሎች መመልከት ሲችል ከዛ ተመልሶ ሲመጣ ጥሩና ሥራ ፈጣሪ ዜጋ ሊሆን ይችላል ሲሉም አመልክተዋል። ከሌሎች የማኅበረሰቡ አካላት ጋር ሲገናኝም፣ የሰከነ፣ ያደገ፣ የሠለጠነ ግንኙነት ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል ያሉት አቶ ኮራ፣ ትምህርት በተግባር የሚያገኙበት አንዱ መንገድ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መሆኑን አመላክተዋል።

የዘንድሮው/ የ2016 ዓ.ም/ የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ንቅናቄ መርሐ ግብር ሰኔ 12 ቀን 2016 ዓ.ም በዓድዋ ሙዚየም በይፋ ተጀምሯል። በዚህ በዓድዋ በተጀመረው የንቅናቄ ማስጀመሪያ መድረክ ላይ የተገኙት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በተደመረ ጉልበት እውቀትና ክህሎት ሀገር የመገንባት ሂደት ነው ሲሉም ገልጸውታል፡፡

ከዚህ ቀደም በበጎ ፈቃድ በተሰጡ አገልግሎቶች የማኅበረሰቡ አንገብጋቢ ችግሮች መፍታት ተችሏል ሲሉ ጠቅሰው፣ በዘንድሮው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሚሊዮኖች ይደገፋሉ ብለዋል፡፡ አነስተኛ በጀት ባለበት ሀገር በበጎ ፈቃድ ሥራዎች ላይ መሳተፍ ያስፈልጋል በማለት፤ ኢትዮጵያ በሚገባት ልክ እንዳልተገኘች የሚያስብ ዜጋ ሁሉ በበጎ ፈቃድ ሠራዎች ላይ ሊሳተፍ እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡

# ስፖርት





## ውስብስቡ የስፖርት አበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነት

**ብርሃን ፈይሳ**

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ ያለው የስፖርት አበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነት በእጅጉ እየሰፋ መምጣቱ ይታወቃል። በአትሌቲክስ ስፖርት ስኬታማ ከሆኑት መካከል የምትመደበው ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጋላጭ በሚል ክትትል የሚደረግባት ሃገር ናት። በእርግጥም ተጠቃሚነቱ በተለያየ ጊዜ ይፋ በሚሆኑ የአትሌቶች የምርመራ ውጤት የተረጋገጠ ሲሆን፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስጋትን ባሳደረ መልኩ ቁጥሩ በመጨመር ላይ ይገኛል።



ይህንን ተከትሎም የኢፌዴሪ ባሕልና ስፖርት ሚኒስትር፣ የኢትዮጵያ ፀረ አበረታች ቅመሞች ባለሥልጣን እንዲሁም የጉዳዩን አሳሳቢነት በተደጋጋሚ በመግለጽ ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ተጨባጭ ውጤት ለማምጣት እየሠሩ ነው። በዚህም በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ባለሙያዎች የጉዳዩን መጠን የሚያመላክት ጥናት ተደርጓል። ጥናቱ የስፖርቱን ባለሙያዎችና ተጠቂ አትሌቶችንም ጭምር ያካተተ ሲሆን፤ በቁጥር የተደገፈ ማስረጃ ቀርቧል። ባለሥልጣኑ በአዋጅ ተቋቁሞ ወደሥራ ከገባበት ጊዜ አንስቶ የሕግ ጥሰት የፈጸሙ አካላትን በማጣራትና አስፈላጊው የእርምት እርምጃ በመውሰድ ላይ ይገኛል።

እስካሁን ድረስም የሕግ ጥሰት ከፈጸሙ 31 አትሌቶች ውስጥ 27ቱን እንደ ጥፋታቸው መጠን ከውድድር አግዷል። የወንጀል ጥፋተኝነትን አስመልክቶ በ5 አትሌቶች፣ 1 ሕገወጥ አዘዋዋሪ፣ 2 የሕክምና ተቋማት እንዲሁም 2 የሕክምና ባለሙያዎች ላይ የክስ አቤቱታ ለፌዴራል ፖሊስ ቀርቦ ክትትል ላይ ይገኛል። 7 በሚሆኑ የመድኃኒት መደብሮችና የሕክምና ተቋማት ላይም አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወስድባቸው ተደርጓል።

ይህ ሁኔታም የሃገርን በጎ ገጽታ ከማጉደፍና የስፖርቱን ተዓማኒነት ከማሳጣት አልፎ እንደሃገር ለከፍተኛ ወጪ እየዳረገም ነው። በኢትዮጵያ የአበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነትን የሚለይ ተቋም ባለመኖሩ ናሙናው ወደ ውጪ ሃገራት ተልኮ ምርመራው እንደሚደረግ ይታወቃል። በዚህም የሽንት እና የደም ምርመራ ለማድረግ እያንዳንዳቸው በአማካይ ከ200 እስከ 270 የአሜሪካ ዶላር የሚጠይቁ ሲሆን፤ ለኤቢፒ ደግሞ ከ40እስከ 50 ዶላር ክፍያ ያስፈልጋል።

ለአብነት ያህል እአአ በ2021 ኢትዮጵያ 63 የደም ምርመራዎችን በራሷ አቅም ስታከናውን ከ12ሺ.600 እስከ 17ሺ.010 የአሜሪካ ዶላር አውጥታለች። ለ765 የሽንት ምርመራዎች ደግሞ ከ153ሺ. እስከ 206ሺ.550 የአሜሪካ ዶላር ከፍላለች። ይህም ምርመራውን ለማከናወን በግብዓትነት የሚገቡ ቁሳቁሶችን 54ነጥብ5 በመቶ ከፍተኛ ታክስን ጨምሮ እንደሆነም ጥናቱ ያመላክታል። በዚህም ከ2010 እስከ 2015 ዓ.ም ከተገኘው ዳሰሳዊ ጥናት ማረጋገጥ እንደተቻለው ወደ ውጪ ሀገር ላብራቶሪዎች የተላኩ ዓመታዊ ናሙናዎች ብዛት 4ሺ.142 ሲሆኑ፤ 2ነጥብ7 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ክፍያ ተደርጓል። ጥናቱ በዝርዝር ካሳያቸው ውጤቶች በመነሳትም በባለድርሻ አካላት ሊከናወኑ ስለሚችሉ ተግባራትም ምክረ ሃሳብ አቅርቧል።

ጥናቱን ተከትሎም የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለሥልጣን ዳይሬክተር መኮንን ይደርሳል፤ አበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነት የዚህ ሃገር ችግር መሆን እንዳልነበረበት ይጠቁማሉ። ባለሥልጣኑ ጥናቱን አሳትሞ በቅርቡ ተደራሽ የሚያደርግ ሲሆን፤ ቀጣዩ ሥራ ደግሞ በጥናቱ የተመላከቱ የመፍትሔ ሃሳቦችን ተግባራዊ ማድረግ ነው። የአበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነት ከጊዜው ጋር እየዘመነና እየጨመረ እንደሚሄድ ታሳቢ ያደረገ ስትራቴጂ ማዘጋጀት የግድ ነው።

ባለስልጣኑ ትኩረቱን ካደረገበት የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ወደ ክትትልና ቁጥጥር ማለፍ ስላለበት ከመጪው በጀት ዓመት አንስቶ የስፖርት ማህበራት የስራቸው አካል እንዲያደርጉት ቅድመዝግጅት እየተደረገ ነው። የጸረ አበረታች ቅመሞችን ባለማወቅ የሚወስዱ አትሌቶች እንዳሉ ሁሉ ተዘጋጅተውበትና በተደራጀ ሁኔታ የሚወስዱ አትሌቶች ቁጥር እየጨመረ ከመሆኑ አንጻር ሥራው ውስብስብና ሰፊ በመሆኑ ባለድርሻ አካላት ሊረባረቡበት እንደሚገባም ነው ዳይሬክተሩ ያስገነዘቡት።

በኢፌዴሪ ባሕልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፤ በበኩላቸው የአበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነት በትውልድ ግንባታ ላይም አደጋን እየደቀነ ያለ ጉዳይ መሆኑን ይገልጻሉ። በተጠቃሚነት ከሚመዘገበው ቁጥር ይልቅ መለመዱ ይበልጥ አደገኛ የሚያደርገው ሲሆን፤ ለሃገርም ሆነ ለዓለም አቀፍ ስፖርት ስጋት ነው። ይህ ወቅት እንደ ኦሊምፒክና ሌሎች አሕጉርና ዓለም አቀፍ ውድድሮች የሚካሄዱበት እንደመሆኑ ግንዛቤውን ማሳደግ ይገባል። በመሆኑም ጥናቱን ሁሉም ባለድርሻ አካላትና የስፖርት ተቋማት በተገኙበት የውይይት መድረክ የሚዘጋጅ መሆኑንና ችግሩን ለመግታት በጋራ የሚሰራ መሆኑንም ነው ያመላከቱት።

## ከፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም



ማሽን ክፍል ሲጎበኝ




አሽከርካሪ ተሽከርካሪ ክፍል ሲጎበኝ

## የአገልግሎቱ አዳዲስ አመራሮች የተለያዩ ክፍሎችን ጎበኙ

**ስሜነህ ደስታ**

የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት በፌዴራል እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ለሚሠሩ ሠራተኞች በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓቶች ከ2007 ዓ.ም. ጀምሮ የሰርቪስ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። ለመንግሥት ሠራተኞች ብቻ ሳይሆን ከሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ውጪ ባሉት ጊዜያት፣ በበዓላት እና በዕረፍት ቀናት ለሌላውም የኅብረተሰብ ክፍል በተመጣጣኝ ታሪፍ የሕዝብ ትራንስፖርት(ታክሲ) አገልግሎት ይሰጣል።

ተቋሙ ከላይ ከተጠቀሱት ተግባራት በተጨማሪ ልዩ የሀገር አቋራጭ ትራንስፖርት አገልግሎት፣ የውጭ ተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት፣ የአሽከርካሪ ማሠልጠኛ፣ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራ ቦሎ፣ የክሬን አገልግሎት፣ የእጥበትና ግሪስ አገልግሎት፣ የጎማና ባትሪ ሽያጭ፣ የተሽከርካሪ ሚዛን አገልግሎት፣ የተሽከርካሪ ሰሌዳና ልዩ ምልክቶች ኅትመት እንዲሁም ሌሎች አገልግሎቶችን እየሰጠ ይገኛል።

በፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት በቅርቡ አዳዲስ አመራሮች ተመድበውለታል። እነዚህ አመራሮች ተቋሙ የሚሰጣቸውን የአገልግሎት ክፍሎች ማለትም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ክፍል ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶችን፣ የአሽከርካሪ ማሠልጠኛ ሲሙሌተር፣ የኢንተለጀንት ትራንስፖርት ሲስተም (አይ ቲ ኤስ)፣ የሠራተኞች ጂምናዚየም፣ የሕፃናት ማቆያ (ዴይኬር)፣ የመኪና አካል መጠገኛ (ቦዲ ክፍል)፣ የተሽከርካሪ ሰሌዳ ምርት አገልግሎት፣ የቴክኒክ አገልግሎት እንዲሁም ምርት ክፍልን በመዘዋወር ጎብኝተዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ አቶ ጥላሁን ጅግሶ እንዲሁም ሌሎች አዳዲስ አመራሮች የተለያዩ አገልግሎት መስጫ ክፍሎችን ሲጎበኙ ከየክፍሉ ሠራተኞች ጋር የተዋወቁ ሲሆን፣ አመራሮቹ በጉብኝታቸው ወቅት በተመለከቱት ሁኔታ እንደተደሰቱ ገልፀዋል። የአገልግሎቱ ዋና ዳይሬክተር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ ጎርፉ ጌታቸውም በጉብኝቱ ማጠናቀቂያ እንኳን ደህና መጣችሁ ዝግጅት በማድረግ አዳዲስ አመራሮችን ከነባር የክፍል ኃላፊዎች ጋር ማስተዋወቃቸውን ከተቋሙ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።